በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ 1980 ዓ.ም የሠፈራ አካባቢዎች ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ

## የቆጣሪዎች መመሪያ

አዲስ አበባ
የካቲት 1980 ዓ.ም

316.3
ETH
MAN

19/4/80

ገጽ


ዓምድ — 16 ማንበብና መጻፍ የማይችሉ የሚችሉ ..... 80

ዓምድ — 17 ብሔረሰብ ..................... 80

ድምር ........................ 81

ጠቅላላ ድምር .................... 81

ዓምድ — 18 ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት ............ 81

ዓምድ — 19 ጠቅላላ የመኖሪያ ቤቶችና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት ... 82

ዓምድ — 20 የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ስም፣ ፊርማና ቀን ........................ 82

ዕዝል 1 ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር ....... 83

ዕዝል 2

2.1 የቤት የቤተሰብና የድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ ቅጽ 1 ...................... 86

2.2 ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ፣ ቅጽ 2 .... 87

2.3 በቆጠራ ጊዜ የቆጣሪ ዕለታዊ የሥራ ከንውን መመዝገቢያ ቅጽ፣ ቅጽ 3 .......... 88

2.4 የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ፣ ቅጽ 4 .... 89

2.5 የሠፈራ አካባቢዎች ያሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ 90

ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ቅ. ገ.ር....... 90

# የሠፈራ አካባቢዎች ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ

## የቆጣሪዎች መመሪያ

## 1. መግቢያ

አስተማማኝ የሆነ ዕቅድና ፖሊሲ ለመተለም እንዲያስችል በአገሪቷ የሚገኘውን የሕዝቡን ብዛት፣ የሕዝቡን የቦሻልና የኢኮኖሚ ሁኔታ ሊያመለከት የሚችል የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ በግንቦት ወር 1976 ዓ.ም. በመላ አገሪቷ ተካሂዷል፡፡ የቆጠራው ውጤት የሚሰጠውን መረጃ አስተማማኝና ወቅታዊ ለማድረግ በየጊዜው የሚከተሉትን ለውጦች በማጥናት እነዚህን ለውጦች ለመለካት ጥረት ይደረጋል፡፡ በአገሪቷ የተካሄደው የሠፈራ ፕሮግራም ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴ በማስከተሉ የዚህን እንቅስቃሴ መጠንና አቅጣጫ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም የሠፈሪውን ሕዝብ መጠንና ሌሎች ባሕሪያትን ማጥናት በሠፈራው አካባቢ ለሚካሄዱ የልማትና የፖሊሲ ውሳኔዎች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱ ሁለት ዓበይት ምክንያቶች የተነሳ ሠፈራ በተካሄደባቸው አካባቢዎችና እንዲሁም ስግስግ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ውስጥ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ይካሄዳል፡፡

## 2. የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ትርጉም

የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በተወሰነ ወቅትና የአስተዳደር ክልል ስለ ሕዝብ ባሕሪያት፣ ስለማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንዲሁም ስለቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ አኃዛዊ መረጃዎች የመሰብሰብን፣ የማጠናቀርንና የመተንተን ከዚያም አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘውን ውጤት የማሰራጨትን ተግባራት ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው ቆጠራው በሕዝብ ወይም በቤቶች ብዛት ላይ ብቻ ባያተኩር ስፋትና ጥልቀት ያሮት የተለያዩ የማሕበራዊና የኢኮኖሚያዊ መስኮች የሚሸፍን ስለ መሆኑ ነው፡፡

1ኛ/ የሕዝቡን ብዛትና ስርጭት በጾታና በዕድሜ እንዲሁም በተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎች ለማስገኘት፣

2ኛ/ የሕዝቡን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ባሕሪያት በሚመለከት መሠረታዊ መረጃዎች ለማቅረብ፣

3ኛ/ የሕዝቡን የልደት፣ ሞትና የፍልሰት መጠን ለማወቅ፣

4ኛ/ ስለቤቶች ብዛትና ስለሚሰጡት አገልግሎት እንዲሁም ስለመኖሪያ ቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ መረጃዎች ለማስገኘት፣

5ኛ/ የብሔረሰቦችን ብዛትና ስርጭት ለማወቅ፣

6ኛ/ ወደፊት ለሚካሄዱ የስታቲስቲክስ ጥናቶች ዝርዝር የሚያገለግሉ መረጃዎች ለማስገኘት ነው፡፡

በእነዚህ ዓላማዎች መሟላት ምክንያት የሚገኙት ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለፖሊሲ ውሳኔ፣ ለተመጣጠነና ለተስተካከለ የልማትና የእድገት ዕቅድ ዝግጅት፣ ለአስተዳደር፣ ለምርምር.... ወዘተ አስፈላጊ ከመሆናቸው በላይ የኅብረተሰቡን የሶሻልና የፖለቲካ ተሳትፎ ለማደራጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማጐልበት፣ አስፈላጊ የሆኑትን የምርቶችና አገልግሎቶች ፍላጎት፣ አቅርቦትና ስርጭት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለመወሰን፣ ስለሰው ኃይል አደረጃጀትና አጠቃቀም ፖሊሲ ለመንደፍ፣ የሕዝቡን የአሰፋፈር ሁኔታ በሚመለከት ተገቢውን ፕሮግራም ለመቀየስ፣ እንደ አስፈላጊነቱ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ነክ እርምጃዎች ለመውሰድ፣ ለአገር እድገትና ብልጽግና የሚያስፈልጉ የልማት ፕሮጀክቶችን በብዛትም ሆነ በዓይነት እንዲሁም ስርጭታቸውን አስመልክቶ ውሳኔ ላይ ለመድረስ፣ ስለመኖሪያ ቤቶች አግባብ ያለው ፖሊሲ ለማውጣትና ፕሮግራም ለማዘጋጀት፣ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ውጤት ታላቅ ሚና አለው፡፡

4. <u>የቆጣሪ አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የሕዝብና ቤቶች ቆጠራን ተግባር የሚያከናውን ቆጣሪ ለቆጠራው ሥራ መሳካት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ስለሆነም ቆጣሪው የቆጠራውን ተግባር በቅንነት፣ በታማኝነት በታታሪነት ማከናወን ይገባዋል፡፡ ቆጣሪ ከተመደበበት የቆጠራ ቦታ ነዋሪ ሕዝብ ጋር ተግባብቶ የቆጠራውን ተግባር ከማከናወኑም በላይ የሕዝቡን ድጋፍና ትብብር ለማግኘት ከአስነዋሪ ድርጊቶች ሁሉ እንዲርቅ ያስፈልጋል፡፡

ቆጣሪው ቆጠራውን ለማካሄድ ወደ የቤተሰቡ በሚደርስበት ወቅት ሰላምታ በመስጠት ራሱን ማስተዋወቅና ስለ መጣበት ዓላማ እንዲገልጽ ያስፈልጋል፡፡ ለቆጠራው መረጃ ስብሰባ ሥራ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በመመሪያው መሠረት መሆን ያለበት መሆኑን በመገንዘብ ለቆጠራው አግባብ የሌለው ጥያቄ መጠየቅ አይኖርበትም፡፡ የቆጠራውን ተግባር ካጠናቀቀ በኋላ ቤተሰቡን አመስግኖ መሰናበት ይገባዋል፡፡

ቆጣሪው ተግባሩን ለማከናወን የተለያዩ መጠይቆችንና ቅጾችን በመሙላት መረጃዎችን ሲመዘግብ ጽሑፉ ንጹሕ፣ የሚታይና የሚነበብ መሆን አለበት፡፡ እንደዚሁም የሞላቸውን ቅጾች ሁሉ በመመርመር አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ ካስፈለገ ወደ ቤተሰቡም በመመለስ በስሕተት የተመዘገቡ፣ የማይመስሉ፣ ለማንበብ የሚያስቸግሩ ... ወዘተ ምላሾችን ማስተካከል አለበት፡፡ ለቆጠራው የሚሰጡትን ዶክሜንቶችና ሌሎች ዕቃዎች በጥንቃቄ መያዝና በቆጠራው የሚሰበስቡትንም መረጃዎች በሚስጢር መጠበቅና ለተቆጣጣሪው በስተቀር ለማንም ግለሰብ ማሳየት አይገባውም፡፡

5. <u>የቆጣሪ ተግባር አፈጻጸም ቅደም ተከተል</u>

ሀ. ለቆጠራው የሚሰጠው የሥልጠና ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ ለቆጠራው አስፈላጊ የሆኑ ዶክሜንቶችና ዕቃዎችን በዝርዝሩ መሠረት ቆጥሮ መረከብ፣

ለ. ወደ ተመደበበት የቆጠራ ቦታ በመሄድ ከቀበሌ ማኅበር [illegible]ጣቢያ
አባላት ጋር ተዋውቆ ከ[illegible] በመሆን [illegible] የቆጠራ
በ[illegible] ቆጠራ ቦታ ድንበር በመዞር
ሳይቱ ማረጋገጥ፣

ሐ. ሥርዓት ባለው መንገድ የቤቶች፣ የቤተሰቦችና የድርጅቶች መዝገብ ማካሄድ፣

መ. የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅቶች ምዝገባ በሚካሄድበት ወቅት ለቤቶች ተከታታይ ተራ ቁጥር በቀይ ጠመኔ በቤቱ በር ከፍ ብሎ በሰተግራ ባለው ጥግ ወይም በር ከሌለው በሚታይና አመቺ በሆነ ቦታ መስጠት፣

ሠ. የቤቶች የቤተሰቦችና የድርጅቶች ምዝገባ ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ከቤት ወደ ቤት በመዞር መሙላት፣ እንደዚሁም የቆጣሪ አስታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት መሙላት፣

ረ. የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ለተሞላላቸው ቤቶችና ቤተሰቦች ቆጠራው የተጠናቀቀ መሆኑን ለመግለጽ በቀይ ጠመኔ በተሰጠው የቤት ቁጥር አቅጣጫ በሰማያዊ ጠመኔ የ"×" ምልክት ማድረግ፣

ሰ. በቤት ሳልተገኙ ቤተሰቦች በቤቱ ለሚጠየቁት ምላሽ የሚሰጥ አዋቂ አባል ባለመገኘት መጠይቁ ሳልተሞላላቸው ቤተሰቦች ተደጋጋሚ ጉብኝት ለማድረግ ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ መሙላት፣

ሸ. በየእለቱ የተሞላውን መጠይቅ በመመርመር፣ መሞላት ሲገባቸው ያልተሞሉ ዓምዶች፣ ሲገናዘቡና ሲመባከሩ ያልቻሉ ዓምዶችና ባይቆጠሩ የተዘለሉ ቤተሰቦች ካሉ ወዲያውኑ ወደ ቤተሰቡ በመሄድ አስፈላጊውን እርማት ማድረግ፣

ቀ. ቆጠራው እንደተጠናቀቀ ለቆጠራው ቦታ የማጠቃለያ ቅጽ መሙላት፣

በ. ቆጠራው በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መጠናቀቁን ተቆጣጣሪው ካረጋገጠ በኋላ አስፈላጊ ዶክሜንቶችና ዕቃዎች ለተቆጣጣሪው ማስረከብ፣

በተቻለ መጠን መረጃው በሚሰበሰብበት ጊዜ መረጃ ሰጪው የቤተሰቡ ኃላፊ እንዲሆን ቢመረጥም የቤተሰብ አባላትን ዝርዝር ሁኔታዎች በሚመለከት በሚረሳበት ጊዜ ከየአባላቱ በቀጥታ ሊሰበሰብ ይቻላል።

አንዳንድ ጊዜ የአንዱን ቤተሰብ መረጃ በመጀመሪያ ጉብኝት ጊዜ ማግኘት አይቻልም ይሆናል። በዚህ ጊዜ ከሦስት ጊዜ ያልበለጠ ተደጋጋሚ ጉብኝት በማድረግ መረጃዎቹ እንዲሰበሰቡ ይሆናል። ከሦስተኛ ጉብኝት በኋላ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ካልተቻለ ሁኔታውን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ ይኖርበታል።

## የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ አሞላል መመሪያ

1. የቅጹ አገልግሎት፡—

ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ ቆጠራ ቦታ ለሚገኙ ቤቶች አገልግሎታቸውን፣ የድርጅቱ ዋና ምርት ወይም ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎትና የቋሚ ሠራተኛ ብዛት፣ የቤተሰብ ኃላፊና በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት መረጃዎች ለመመዝገብ ያገለግላል። ቅጹ በሁለት የተከፈለ ሲሆን ክፍል አንድ የአካባቢ መለያ መመዝገቢያ ሆኖ ክፍል ሁለት የቤት የቤተሰብና የድርጅት መመዝገቢያ ነው።

2. የምዝገባው ዓላማ፡—

የምዝገባው ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. በአካባቢው ያሉትን ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶችን ብዛት ለማወቅ፣

ለ. ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት ቤቶችና ቤተሰቦች እንዳይዘለሉና ተደጋግመው እንዳይቆጠሩ ለመቆጣጠር፣

ሐ. የቤቶች የቤተሰቦችና የድርጅቶች ዝርዝር በማዘጋጀት ወደፊት ለሚከናወኑ የሶሻልና የኢኮኖሚ ጥናቶች የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት።

3. የምዝገባው አፈጻጸም፡—

ምዝገባው በሚካሄድበት ወቅት የሚከተሉት ተግባራት መፈጸም አለባቸው።

ሀ. በመጀመሪያ የቆጠራ ቦታውን ድንበር ዙሮ ማየትና ማጥናት፣

ለ. የቤቶችን የመንገዶችንና የመንደሮችን አቀማመጥ ማየት፣

ሐ. የቆጠራ ቦታን በዞኖች /በሠፈሮች/ መሸንሸን

መ. ምዝገባውን በቆጠራው ቦታ ሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው መንደር /ዞን/ በመነሳት ወደ ምሥራቅ ሥርዓት ባለው መንገድ በመጓዝ እያንዳንዱን ቤት፣ ቤተሰብና ድርጅት በቅደም ተከተል መመዝገብ፤

ሠ. ምዝገባው የሚከናወነው በያንዳንዱ መንደር /ዞን/ የሚገኙትን ቤቶች ቤተሰቦችና ድርጅቶች መዝገብ ከጨረሰ በኋላ ወደሚቀጥለው መንደር /ዞን/ በመሸጋገር ይሆናል፤

ረ. ከመጀመሪያው ቤት ጀምሮ በቀይ ጠመኔ በቤቱ በር ከፍ ብሎ በስተግራ ባለው በር ጥግ ወይም በር ከሌለው አመቺ በሆነና ዝናብና ልጆች ሊያጠፉት በማይችሉበት ቦታ ተከታታይ የቤት ተራ ቁጥር ይሰጣል።

ሰ. ምዝገባ ተጠናቅቆ ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ ከመጀመሪያው ቤት በመጀመር ለተቆጠረ ቤት የተቆጠረ መሆኑን ለማመልከት በሰማያዊ ጠመኔ በቤቱ ቁጥር አንፃር የ"x" ምልክት ይደረግበታል።

ሸ. ምዝገባው በሚካሄድበት ጊዜ በጫካ ውስጥ የሚገኙና በቀላሉ ሊታዩ የማይችሉ ቤቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ጠይቆ ማግኘትና መመዝገብ ያስፈልጋል፤

ቀ. የምዝገባው ሥራ ተጠናቀቀ የሚባለው በቆጠራው ቦታ ውስጥ የሚገኙት ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች በሙሉ ሲመዘገብ ነው።

<u>የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ቅጽ አሞላል መመሪያ፤</u>

ክፍል - 1 <u>የአካባቢ መለያ</u>

ከዓምድ 1 - 8 ባሉት ዓምዶች የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት የአካባቢ መለያ መረጃ ይሞላል።

ዓምድ - 1 <u>ክፍለ ሀገር</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ክፍለ ሀገር ስም ይመዘገባል።

ዓምድ — 2 <u>አውራጃ</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት አውራጃ ስም ይመዘገባል።

ዓምድ — 3 <u>ወረዳ</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ወረዳ ስም ይመዘገባል።

ዓምድ — 4 እና 5 <u>ከተማና ከፍተኛ</u>

ይህ ዓምድ አይሞላም።

ዓምድ — 6 <u>የመቁጠሪያ ቦታ</u>

ይህ ዓምድ አይሞላም።

ዓምድ — 7 <u>የገበሬ ማኅበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ</u>

ቤተሰቡ የሚኖርበት የገበሬ መኅበር ወይም ሠፈራ ጣቢያ ስም በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተመዝግቦ ኮዱ ቁጥር በዚህ ዓምድ ከ13—15 ባሉት ኮለሞች ይሞላል።

ዓምድ — 8 <u>የቆጠራ ቦታ</u>

ይህ ዓምድ አይሞላም።

ክፍል—2 <u>የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ሁኔታ</u>

ዓምድ — 9 <u>የቤት ተራ ቁጥር</u>

በቆጠራው ቦታ ለሚገኙ ቤቶች ኣንዷ አመዘጋገባቸው ቅደም ተከተል ተከታታይ ተራ ቁጥር 001፣ 002፣... ወዘተ በመስት ቤቶቹ ተመዝግበው ኣስከአለቀ ድረስ በዚህ ዓምድ በካርዱ ኮለም 18—20 ይሞላል። እነዚህ በካርዱ ኮለም 18—20 የተመዘገቡት ተራ ቁጥሮች በቤቱ በር ከፍ ብሎ በስተግራ ባለው ጥግ ወይ– በር

ከሌለው አመቺ በሆነና ዝናብና ሌሎች ሲያጠፉት በማይችሉበት ቦታ በቀይ ጠመኔ መጻፍ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ቤት ሁለትና ከዚያ በላይ ቤተሰቦች /የቤተሰብ ትርጉም ለዓምድ 10 በተሰጠው መግለጫ ተገልጿል/ ከኖሩበት የነዚህ ቤተሰቦች ኀላፊዎች በዓምድ 17 በየተራ በሚመዘገቡበት ጊዜ የቤቱ ተራ ቁጥር በዓምድ 9 ተደጋግሞ መጻፍ ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፎቅ በሆነ ቤት ውስጥ አራት መኖሪያ ቤቶች ካሉ ለአራቱም የቤት ተከታታይ ተራ ቁጥር በዓምድ 9 መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አነጋገር በአንድ አጥር ግቢ አንድ ቤተሰብ የሚኖርባቸው ከአንድ ቤት በላይ ቢኖሩ አንድ የቤት ተራ ቁጥር ለዋናው ቤት የሚሰጥ ሲሆን ከአንድ በላይ ቤተሰብ የሚኖርባቸው ከሆነ ግን ለያንዳንዱ ተከታታይ የቤት ቁጥር መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ — 10 የቤት ቁጥር

የቤት ቁጥር በዓምድ 10 ከመመዝገቡ በፊት፣ የቤት፣ የመኖሪያ ቤትና የቤተሰብ ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ሀ. ቤት

ቤት ማለት በአሠራሩ ተለይቶ "ራሱን የቻለ" ሆኖ ለመኖሪያ ብቻ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ወይም ለድርጅቱ ብቻ የሚያገለግል ነው፡፡

የቤቱ አሠራር የተለየ ነው

የሚባለው ዙሪያውን በግድግዳ፣ በአጥር ግቢ...ወዘተ የተከለለ ሆኖ ጣሪያም በኮዳን የተሸፈነ በመሆኑ በውስጥ የሚኖሩት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ፣ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ከሌሎች በዙሪያው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በሳጠራ፣ በኘላስቲክ፣ በካርቶን፣...ወዘተ ግድግዳው የተሠራ ወይም ጣራው በኘላስቲክ ኮዳን የተሸፈነ ሆኖ ለድርጅት ወይም ለመኖሪያ የሚያገለግል

ቤት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ምንም እንኳን የቤትን ትርጉም ባያሟላም ከአገልግሎቱ አንጻር ሲታይ ቤት ስለሆነ እንደቤት ይወሰዳል፡፡

<u>የቤቱ አሠራር ራሱን የቻለ ነው</u>

የሚባለው ቤቱ ከመንገድ ወይም የጋራ በሆነ ደረጃ፣ መሬት ...ወዘተ የራሱ መግቢያና መውጫ ያለው ሆኖ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ወደ ቤት ሲገቡ ወይም ከቤት ሲወጡ የሚተላለፉት በሌሎች ቤት ውስጥ በማለፍ ሳይሆን በቀጥታ በራሳቸው ቤት መውጫ ወይም መግቢያ ብቻ ሲሆን ነው፡፡

ለ. <u>መኖሪያ ቤት</u>

መኖሪያ ቤት ማለት ሙሉ በሙሉ ሰዎች የሚኖሩበት ወይም በከፊል እየኖሩ በቀረው ሌላ ተግባር ለምሳሌ ንግድ፣ ሽመና፣ የእንጨት ሥራ ...ወዘተ የሚያከናውኑበት ቤት ማለት ነው፡፡ የመኖሪያ ቤት ለሰው መኖሪያ ተብሎ የተሠራ ወይም የተዘጋጀ ሳይሆን በቆጠራው ጊዜ እንደ መኖሪያ የሚያገለግል ሊሆን ይችላል፡፡

ሐ. <u>ቤተሰብ</u>

ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማድ ቤት አብስለው በአንድነት የሚመገቡ ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡ የቤተሰብ አባሎች በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች፣ የባል ወይም የሚስት አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም፣...ወዘተ ሲሆኑ በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱት ሌሎች የቤተሰብ አባላት ናቸው፡፡ የቤተሰብ አባላት በቤት ሠራተኛነትና በዘበኝነት የሚያገለግሉትንም ይጨምራል፡፡

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ወይም ሌሎች ሰዎች እንደ ዘበኞች፣ ጥገኞች፣...ወዘተ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ፡፡ ነገር ግን ቆጠራው ከሚፈጸምበት ቀን በፊት ቤተሰቡን ትቶ ለኣንግዱነት ወደ ሌላ ቤተሰብ በመሄዱ ኣዚያ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው፡፡

ጋብቻው በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤተሰብ ባልን፣ ሚስትን፣ ልጆችን፣ የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን /የቤት ሠራተኞች ...ወዘተ/ ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ /አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ከአሉት/ የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ...ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩ፣ ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ፣ በቅድሚያ ካገባት ሚስቱ በስተቀር ኣያንዳንዳቸው የሰውየው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ ኣንዳላቸው ሆኖ መቆጠር አለባቸው፡፡ ባልየው ደግሞ በቅድሚያ ከአገባት ሚስቱ ጋር ኣንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ለቤት፣ ለመኖሪያ ቤትና ለቤተሰብ የተሰጠውን ትርጉም በሚገባ በመገንዘብ የቤት ቁጥር በዓምድ 10 ይሞላል፡፡ በቆጠራው ቦታ ለሚገኙ ለአብዛኞቹ ቤቶች በቀበሌው ጽሕፈት ቤት የመለያ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ የሆኑ የተለያዩ ቁጥሮች ያሉዋቸው መኖሪያ ቤቶች ሊይዝ ይችላል፡፡ ኣንዲሁም ደግሞ በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የቤት ቁጥር በዚህ ዓምድ ከመሞላቱ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች በጥሞና ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

1. በአንድ መኖሪያ ቤት ከአንድ በላይ ቤተሰቦች የሚኖሩበት ከሆነ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በሚሞላው መጠይቅ የዚህ የመኖሪያ ቤት ቁጥር በተደጋጋሚ በዓምድ ይሞላል፡፡

2. አንድ ቤተሰብ ከአንድ በላይ የሆኑና የተለያዩ ቁጥሮች የተሰጣቸው የመኖሪያ ቤቶች ከያዘ ቤተሰቡ የሚኖርበት የዋናው ቤት ቁጥር፣ ወይም በመታወቂያ ወይም በራሽን ካርድ የተሞላው የቤት ቁጥር በዓምድ 10 በካርድ ኮለሞች 21–24 ይሞላል፡፡

3. ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሱት ትናንሽ ቤቶች /"ሰርቪስ"/ በተለያዩ ቤተሰቦች የተያዙ ኣንደሆነና የትልቁ ቤት ተቀጽላ ቁጥር የተሰጣቸው ከሆነ በዓምዱ በተሰጠው ቦታ የትልቁን ቤት ቁጥር በመሙላት ቤቶቹ የትልቅ ቤት ተቀጥላዎች መሆናቸውን በአስተያየት ዓምድ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ትናንሾቹ /ሰርቪሶች/ የተለያዩ የራሳቸው ቁጥር በቀበሌው ጽሕፈት ቤት ከተሰጣቸው ይህንኑ ቁጥር በዓምድ 10 በካርድ ኮለሞች 21–24 መሙላት ያስፈልጋል፡፡

4. በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኝ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ መኖሪያ ቤቶች ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ቤተሰቦች ተይዘው የተሰጠውን የመኖሪያ ቤት ቁጥር ግን ለግቢው የሚያገለግል አንድ ቁጥር ብቻ ከሆነ ይኸው ቁጥር ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በዓምድ 10 በእያንዳንዱ ቤት አቅጣጫ መመዝገብ አለበት፡፡ እነዚህ ተደጋጋሚ የቤት ቁጥሮች ለግቢው የተሰጡ መሆናቸውን በአስተያየት ዓምድ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡

5. ቤቱ በቆጠራው ቀን ቁጥር የሌለው ከሆነ ዓምዱ ባዶ ይተዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቀበሌዎች በዞን የተከፈሉ ሲሆን የቤት ቁጥር አሰጣጥም በዞኖች የተመሠረተ መሆኑ የቤቶች ቁጥር ሊደጋገም ይችላል፡፡ ይኸም ማለት ለምሳሌ በዞን አንድ የቤት ቁጥር 001 ቢኖር በዞን 2፣ 3፣...ወዘተ

ቁጥራቸው 001 የሆኑ ሌሎች ቤቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሁኔታ ሊያጋጥምና የቤቶችም ቁጥር ተደጋግሞ ሊጻፍ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የእያንዳንዱ ዞን ስም በአስተያየት ዓምድ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ — 11 <u>የቤት ንዑስ ቁጥር</u>

ቤቱ በተለያዩ ንዑስ ቤቶች ወይም መኖሪያ ቤቶች ተከፋፍሎ የተለያዩ ቤተሰቦች የሚኖሩበት ሊሆን ይችላል፡፡ ለነዚህ ንዑስ ቤቶች ወይም መኖሪያ ቤቶች ከዋናው ቤት ቁጥር ቀጥሎ ለእያንዳንዳቸው ንዑስ ቁጥር በቀበሌው ተሰጥቶ እንደሆነ እነዚህ ንዑስ ቁጥሮች በዓምድ 11 በካርድ ኮለሞች 25 — 27 ይመዘገባሉ፡፡ ለምሳሌ የፎቁ ቤት ዋና ቁጥር 50 ሆኖ በውስጥ አራት ቤቶች ሲኖሩት ለእያንዳንዱ ቤት 001፣ 002፣ 003 እና 004 ንዑስ ቁጥሮች ይሰጣቸዋል፡፡ በዓምድ 11 በተከታታይ ከዋናው ቤት ቁጥር አንጻር የሚመዘገቡትም እነዚህ ከ001 — 004 ያሉት ንዑስ ቁጥሮች ናቸው፡፡ እንዲሁም በአንድ ግቢ ውስጥ ባሉ ብዙ ቤቶች የተለያዩ ቤተሰቦች ከኖሩበት ለግቢው ራሱን የቻለ ቁጥር ተሰጥቶ በግቢው ውስጥ ላሉት ቤቶች ለእያንዳንዳቸው የተለያዩ ቁጥሮች ተሰጥተዋቸው ከሆነ እነዚህ ቁጥሮች እንደ ንዑስ ቁጥር ተወስደው በዚህ ዓምድ ይመዘገባሉ፡፡ ንዑስ ቁጥሮቹ በፊደል የተሰጡ ከሆነ ፊደሎቹን ወደ አሀዝ በመለወጥ በዓምዱ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የቤት ቁጥር በውስጡ ሁለት ቤቶች ኖረው ለእያንዳንዱ ቤት "ሀ" እና "ለ" የሚል ንዑስ ቁጥር የተሰጣቸው ቢሆን፣ በፊደል የተሰጠውን ንዑስ ቁጥር ወደ አሀዝ በመለወጥ "001"፣ "002" በሚሉ ንዑስ ቁጥሮች መተካት ያስፈልጋል፡፡ ቤቱ ንዑስ ቁጥር ከሌለው በዚህ ዓምድ ምንም አይመዘገብም፡፡

ዓምድ — 12 <u>የቤቱ አገልግሎት</u>

በዚህ ዓምድ ከዓምድ 9—11 የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል:: የአገልግሎት ዓይነቶችና ኮዶቻቸው ከዚህ ቀጥሎ ተዘርዝረዋል::

1 = ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ

2 = ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት

3 = ለሆቴል

4 = ለሆስቴል

5 = ለሌላ ጋርዮሽ

6 = ለሌላ ድርጅት ብቻ

7 = ያልተያዘ

8 = በመሠራት ላይ ያለ

ከዚህ ቀጥሎ ለእያንዳንዱ የቤት አገልግሎት ዓይነት ትርጉምና የአመዘጋገቡ ሁኔታ ተሰጥቷል::

1. <u>ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የዋለ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ" ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ የኮድ ቁጥር "1" በካርዱ ኮለም 28 ይሞላል::

2. <u>ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ደግሞ ለድርጅት አገልግሎት የዋለ እንደሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ ቤተሰብ መኖሪያና ለድርጅት" ተብሎ ይመዘገብና ኮዱ "2" በካርዱ ኮለም 28 ይሞላል:: ከዚህ ቀጥሎ የድርጅት ትርጉም ተሰጥቶአል:: ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚለው ሆቴል፣ ሆስቴልና ሌላ ጋርዮሽን አይጨምርም::

ድርጅት

ድርጅት ማለት በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ የቦሻል ወይም የኢኮኖሚ ተቋም ነው:: ይኸውም የማምረቻ፣ የአገልግሎትና የንግድ ተቋሞችን ያጠቃልላል:: ለምሳሌ ጫማ፣ ዳቦ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ... ወዘተ አምራቾች፣ የጫማ አዳባት፣ የትራንስፖርት፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሕግ፣ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት እና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ የሚያካሂዱትን ሁሉ ያጠቃልላል::

ከላይ በተሰጠው የድርጅት ትርጉም መሠረት የቤቱ አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚባለው በአንድ ቤት ውስጥ የቤተሰብ አባላት እየኖሩበት እዚያው ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት የድርጅት ዓይነቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተግባራት ሲያከናውኑበት ነው:: ይኸውም ለምሳሌ:-

ቤቱ ለመኖሪያና ለመጠጥ መሸጫ /ጠላ፣ ጠጅ ሌሎች መጠጦች/
" " ለምግብ መሸጫ
" " ለሸመና
" " ለንግድ /ኪዮስክ/
" " ለሸክላ ሥራ
" " ለብረታ ብረት ሥራ
" " ለጫማ ሥራና ጥገና

በቤቱ ውስጥ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ባለቤቶች የማይኖሩበት ቢሆንና ነገር ግን ሠራተኞች የሚኖሩበት ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት ተብሎ ይመዘገባል::

3. <u>ሆቴል</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለሆቴል ብቻ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለሆቴል ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 3 ይምሳል፡፡ በሆቴል ውስጥ በቤተሰብ መልክ የሚኖር እንደ ሆቴል ነዋሪ እንጂ እንደ ቤተሰብ አይቆጠርም፡፡

ሆቴል:— ማለት የምግብ፣ ወይም የመጠጥ [illegible] ወይንም ሁሉም የሚሰጥ ድርጅት ነው፡፡

4. <u>ሆስቴል</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለሆስቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሆስቴል" ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር "4" ይምሳል፡፡

ሆስቴል:— ሆስቴል ማለት ብዙ ሰዎች ከመደበኛ ቤተሰብ አኗኗር ውጪ በአንድ ቤት ወይም ቤቶች በአንድነት ኣየኖሩ በቤቶም ያሉ ትን መገልገያዎች ማለት ውሃን፣ መብራትንና ሌሎች አገልገሎቶችን በጋራ ወይም በኅብረት የሚጠቀሙትን በአንድ ድርጅት ሥር የሚተዳደሩበት የጋርዮሽ መኖሪያ ሥፍራ ነው፡፡

5. <u>ሌላ ጋርዮሽ</u>

ሌላ ጋርዮሽ የሚባሉት ከሆቴልና ከሆስቴልበስተቀር ሌሎችን የጋርዮሽ መኖሪያ ሥፍራዎችን በሙሉ የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡

ይኸውም:— ወህኒ ቤቶች፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶች፣ ሕፃናት ማሳደጊያ፣ ሆስፒታሎች
የወታደር ካምፕ፣ ያረጁ ሰዎች መጠሪያዎች፣ ፖሊስ ጣቢያ ኣሥር ቤት ካሳቸው፣ የፀበይ ማረሚያዎች፣ አድባራትና ገዳማት፣ የሠራተኛ ካምፖች፣...ወዘተ ናቸው፡፡

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከሆነ የቤት አገልግሎት "ሌላ ጋርዮሽ" ተብሎ በዓምዱ 12 ይመዘገብና በካርዱ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 5 ይሞላል።

6. ሌላ ድርጅት

ሌላ ድርጅት የሚባሉት ሆቴሎች፣ ሆስቴሎችና "ሌላ የጋርዮሽ" መኖሪያዎች ባይጨመሩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የሚያጠቃልሉ ናቸው።

ይኸውም፦ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የማምረቻ ድርጅቶች፣ የንግድ ተቋሞች፣ ቤተ ክርስቲያኖችና መስጊዶች /የግለሰቦችን የጸሎት ቤቶች አይጨምርም/፣ መኝታ ቤት የሌላቸው ቡና ቤቶች፣ መኝታ ቤት የሌላቸው ግሮሰሪዎች፣ ጋራዥ፣ መጋዘን፣ ትምህርት ቤት፣....ወዘተ

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ሌላ ድርጅት" ተብሎ በዓምዱ 12 ይመዘገብና በካርዱ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 6 ይሞላል።

7. ያልተያዘ

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን በሆነ ምክንያት በአገልግሎት ላይ ያልዋለ እንደሆነ "ያልተያዘ" ቤት ተብሎ በዓምዱ 12 ይመዘገብና በካርዱ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 7 ይሞላል።

8. በመሥራት ላይ ያለ

በመሥራት ላይ ያለ ቤት ማለት ቢያንስ ግድግዳው የቆመ ወይም ያለቀ ወይም ጣሪያው ያለቀ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ተሠርቶ ያልተጠናቀቀ ማለት ነው። የሚመዘገበው ቤት በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ከሆነ "በመሥራት ላይ" ተብሎ በዓምዱ 12 ይመዘገብና በካርዱ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 8 ይሞላል።

ነገር ግን በመሠረት ላይ ያለ ቤት በቆጠራው ወቅት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ የአገልግሎቱ ዓይነት በዓምዱ ይመዘገባል። ለምሳሌ በመሠረት ላይ ያለ ቤት ለመደበኛ መኖሪያ በመገልገል ላይ ካለ ለመደበኛ መኖሪያ ተብሎ ይመዘገባል። እንዲሁም ለድርጅት በመገልገል ላይ ካለ የድርጅቱን ዓይነት መመዝገብ ነው። ይኸውም ሆቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለሆቴል፣ ለሆስቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሆስቴል፣" ወይም ለሌላ ድርጅት ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሌላ ድርጅት" ተብሎ ይመዘገባል።

ዓምድ 13–15 <u>ቤቱ ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት፣ ለሆቴል፣ ለሆስቴል፣ ለሌላ ጋርዮሽ ወይም ለሌላ ድርጅት ከሆነ</u>

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት ቤቱ በቆጠራው ቀን ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት፣ ለሆቴል፣ ለሆስቴል፣ ለሌላ ጋርዮሽ ወይም ለሌላ ድርጅት የሚያገለግል ከሆነ ነው።

ዓምድ – 13 <u>ስም ወይም የባለቤቱ ስም</u>

ይህ ዓምድ በቆጠራው ቀን የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያና ለድርጅት፣ ለሆቴል፣ ለሆስቴል፣ ለሌላጋርዮሽ ወይም ለሌላ ድርጅት ከሆነ የሆቴሉ፣ የሆስቴሉ፣ የሌላ ጋርዮሽ ወይም የሌላ ድርጅት ሕጋዊ ስም ወይም ሌላ ድርጅቱ የሚታወቅበት ስም ወይም ስም ከሌለው የባለቤቱ ስም በዓምድ 13 ይመዘገባል።

ዓምድ – 14 <u>ዋና ምርት፣ የሚሰጠው አገልግሎት ወይም የንግድ ዓይነት /የችርቻሮ ወይም ጅምላ ንግድ/</u>

ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎት ወይም የሚያመርተው ምርት ወይም የንግድ ዓይነት በዓምድ 14 ይመዘገባል። የንግድ ዓይነት ችርቻሮ ንግድ ከሆነ ችርቻሮ ንግድ፣ ጅምላ ሽጭ ከሆነ ጅምላ ሽጭ ተብሎ ይመዘገባል።

ከአንዱ በላይ የንግዱ፣ የምርትና የአገልግሎት ዘርፍ ካጋጠመ በሚያስገኘው ገቢ መጠን መሠረት ዋናው የዘርፍ ዓይነት ይመዘገባል:: ከዚህ ቀጥሎ የምርት፣ የአገልግሎትና የንግድ ትርጉም ተሰጥቷል::

ምርት:— የዕቃዎችንና የሸቀጣሸቀጦችን ቅርጽና ይዘት የሚለውጥ ተግባር ማምረት ይባላል:: በግብርና፣ በመዕድንና በድንጋይ ቁፋሮ፣ በማምረቻ ድርጅት፣ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ጋዝና ውኃ፣ እንዲሁም ኮንስትራክሽን ሥራ የተሰማሩትን የማምረቻ ድርጅቶች ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን የነዚህ ዓይነት ድርጅቶች ዋና ምርት በዓምድ 14 ይመዘገባል::

አገልግሎት:— የተዘጋጀ ምግብና መጠጥ መሸጥ፣ መኝታ ቤት ማከራየት፣ የትራንስፖርት ድርጅቶች፣ የኢንጂነሪንግ፣ የቅየሳና የንድፍ፣ ማስታወቂያና ፎቶ ኮፒ፣ የፖስታ፣ የቴሌግራፍ፣ የቴሌፎን፣ የቴሌክስ አገልግሎት፣ የመጋዘን፣ የገንዘብና የመድን፣ የሂሣብና የኦዲት ሥራን፣ የሕግ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የኃይማኖት፣ ሲኒማና ቴአትር፣ ለቤተሰብ የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ጥገናና እንክብካቤ የመሳሰሉትን አገልግሎቶችን ያጠቃልላል:: ልብስ ቀርቦላቸው ያገለግሎት ዋጋ በማስከፈል የሚሰፉ አገልግሎት ዘርፍ ሲመደቡ ልብስ ከራሳቸው ሆኖ ሰፍተው ለነጋዴ የሚሸጡ ሁሉ በአምራች ዘርፍ ይመደባሉ:: የአገልግሎቱ ዓይነት በዓምድ 14 ይገለጻል::

ንግድ:— የዕቃዎችንና የሸቀጣ ሸቀጦችን ቅርጽና ይዘት ሳይለውጥ ገዝቶ የመሸጥ ተግባር ንግድ ይባላል:: የንግድ ዓይነት ሁለት ሲሆን አንደኛው የጅምላ ሻጭነት ሲሆን ሁለተኛው የችርቻሮ ንግድ ነው:: የንግድ ወኪሎችና ደላሎች በንግድ ሥራ ውስጥ ይመደባሉ:: የንግድ ዓይነት በዓምድ 14 ይመዘገባል::

ዓምድ — 15 የቋሚ ሠራተኞች ብዛት

ቋሚ ሠራተኛ መለት ዕድሜው 10 ዓመትና ከዛ በላይ የሆነ ደመወዝ ተከፍሎት ሆነ ሳይከፈለው በሆቴሉ፣ በሆስቴሉ፣ በሌላ ጋርዮሽ ወይም በሌላ ድርጅት በሥራ ተካፋይ የሆነ ባለንብረት፣ በሥራው ተካፋይ የሆኑ የባለ ንብረቱ ቤተሰብ አባላት፣ ሸሪኮችና በደመወዝ ተቀጥረው የሚሠሩትን ቋሚ ሠራተኞች ያጠቃልላል:: ነገር ግን በሠራተኛውና በአሠሪው መካከል በተደረገ የቃል ወይም የጽሑፍ ስምምነት መሠረት የቅጥር ሁኔታው ሲቋረጥ የሚችለውን ጊዜአዊ ሠራተኛ አይጨምርም:: በቆጠራው ቀን በሆቴሉ፣ በሆስቴሉ በሌላ ጋርዮሽ ወይም በሌላ ድርጅት በመሥራት ላይ የሚገኙትን ቋሚ ሠራተኞች ብዛት በዓምድ 15 በካርድ ኮለም ከ32–35 ይመዘገባል::

ድርጅቱ ቅርንጫፍ ከሆነ የቋሚ ሠራተኞች ብዛት የዋናውን ሳይጨምር የቅርንጫፉን ቋሚ ሠራተኞች ብቻ ያመለክታል:: አንድ ድርጅት /ጠላ ቤት፣ ሱቅ...ወዘተ/ ተጨማሪ ቋሚ ሠራተኞች በደሞዝ ሳይቀጥር በባለቤቱ ብቻ የሚካሄድ ከሆነ ድርጅቱ አንድ ቋሚ ሠራተኛ /ይኸውም ባለቤቱ/ እንዳለው ይቆጠራል::

ዓምድ — 16 የቤተሰብ ኃላፊ ተራ ቁጥር

በዚህ ዓምድ በቆጠራው ቀን ቤቱ ለመኖሪያ ብቻ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ከሆነ በዓምድ 17 ለተመዘገቡ የቤተሰብ ኃላፊዎች ተከታታይ ተራ ቁጥር ከ36–37 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሰጣል:: ለቤተሰብ ኃላፊ ተራ ቁጥር አሰጣጥ 001፣ 002፣ ...ወዘተ እየተባለ በቆጠራው ቦታ ያሉ የቤተሰብ ኃላፊዎች ተመዝግበው እስከ ተጠናቀቁ ድረስ ይሆናል:: የቤተሰብ ትርጉም ቀደም ብሎ በዓምድ 10 ለቤት ቁጥር አምሳል በተሰጠው መመሪያ ሥር የተሰጠ ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ የቤተሰብ ኃላፊ ትርጉም ይሰጣል::

የቤተሰብ ኃላፊ:— "የቤተሰብ ኃላፊ" ማለት የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሆነ ወንድ/ሴት በቤተሰቡ አባላት ዘንድ ኃላፊ የሚቆጠር/የሚታይ ነው:: ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ሚስቶቹ በተለያዩ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ እሱ የቤተሰቡ ኃላፊ ሆኖ የሚመዘገበው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት /አንጋፋ/ ሚስቱ ጋር ይሆናል:: ሌሎች ሚስቶች ግን የየራሳቸው ቤተሰብ ኃላፊ ሆነው ይመዘገባሉ::

ዓምድ — 17 <u>የቤተሰቡ ኃላፊ ስም</u>

በዚህ ዓምድ በቆጠራው ቀን ቤቱ ለመኖሪያ ብቻ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ለሆነ የቤተሰብ ኃላፊ ስም ይመዘገባል:: በዓምድ 16 የተሰጠውን የቤተሰቡ ኃላፊ ትርጉም መሠረት በማድረግ የቤተሰቡን ኃላፊ ስም በዓምዱ መመዝገብ ያስፈልጋል:: በአንድ ቤት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች በደባልነት የሚኖሩ ከሆነ የእያንዳንዱ የቤተሰብ ኃላፊ ስም የተለያየ የቤተሰብ ተራ ቁጥር ተሰጥቶት በየተራ በዓምዱ መመዝገብ አለበት:: ስለዚህ በቤቱ ውስጥ ስንት ቤተሰቦች እንደሚኖሩ በቅድሚያ መጠየቅ ያስፈልጋል::

ዓምድ — 18 <u>በግብርና ብቻ ወይም በከፊል ግብርና የተሰማሩ የቤተሰብ አባል አሉ? ካሉ የግብርናው ዓይነት ምንድን ነው?</u>

በቅድሚያ ቤተሰቡ በግብርና የተሰማራ መደበኛ አባል ካለ የቤተሰቡን ኃላፊ መጠየቅ ያስፈልጋል:: በግብርና የተሠማራ መደበኛ የቤተሰብ አባል በቤተሰቡ መኖሩ ከተረጋገጠ የተሰማራበት የግብርና ዘርፍ ምን እንደሆነ ጠይቆ አባሉ የሰጠውን መልስ በዓምዱ መመዝገብ ያስፈልጋል:: ከዚያም ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ኮዶች ትክክለኛ የሆነውን ኮዱ በመምረጥ በዓምድ 18 በካርድ ኮለም 39 ይጻፋል::

1 = ሰብል ብቻ /በሬ ወይም ሌላ እንስሳ ሳይጠቀሙ በቁፋሮ ወይም በሌላ ዘዴ ቡና፣ ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ጫት፣ እንሰት፣ በቆሎ ... ወዘተ የሚያመርቱ:: በትራክተር እያረሱና ሰብል ብቻ የሚያመርቱ በዚህ ይመደባሉ::

2 = ከብት እርባታ ብቻ /ምንም ሰብል ሳያመርቱ ከብት ብቻ የሚያረቡ/

3 = ሌላ ግብርና /ዶሮ እርባታ፣ ንብ እርባታ፣ ዓሣ መስገር፣ ከሰል ማክሰል፣...ወዘተ/

4.= ሰብልና ከብት እርባታ /ሰብል እያመረቱ አንድ ከብት ወይም ከዚያ በላይ የሚያረቡ/

5 = ሰብልና ሌላ ግብርና

6 = ከብት እርባታና ሌላ ግብርና

7 = ሰብል፣ ከብት እርባታና ሌላ ግብርና

ዓምድ — 19 <u>አስተያየት</u>

ይህ ዓምድ መዝገቡ በሚከናወንበት ወቅት ከመዝገቡ ጋር ግንኙነት ያላቸው ችግሮች/ሌሎች ሁኔታዎች ያጋጠሙ እንደሆነ ይመዘገብበታል::

<u>ማሳሰቢያ</u>

<u>ለሆቴልና ለሆስቴል ነዋሪዎች፣ ለሌላ ጋርዮሽ ነዋሪዎች እንደዚሁም ቤት ለሌላቸው ግለሰቦች እንደ መደበኛ ቤተሰብ አባላት የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች መጠይቅ ይሞላ
ላቸዋል:: መጠይቆቹ በሚሞሉበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል::</u>

ሀ. <u>የሆቴል፣ የሆስቴልና የሌላ ጋርዮሽ ነዋሪዎችን በሚመለከት</u>

በዓምድ 9 የነዋሪው ዓይነት በሚመለከት የሆቴልና የሆስቴል ወይም ሌላ ጋርዮሽ ነዋሪ ለሚለው የተሰጠው መልስ ኮድ በካርድ ኮለም 23 ውስጥ ለተሞላላቸው

በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ውስጥ የሚከተሉት ዓምዶች ወይም ክፍሎች አይሞሉም፡፡ ማንኛውም በሆቴሉ ወይም በሆቴሉ አጥር ግቢ በቤተሰብ ወይም በሆቴል የአኗኗር ስርዐት የሚኖር እንደሆቴሉ ነዋሪ ተወስዶ መጠይቁን ይሞላለታል፡፡

1ኛ/ ክፍል አንድ ዓምድ 13 የቤተሰብ ተራ ቁጥር አይሞላም፡፡

2ኛ/ ክፍል አራት ስለ መኖሪያ ቤቶች ዝርዝር መረጃ አይሞላም፡፡

ነገር ግን በዓምድ 17 "ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና" በሚመለከት ለእያንዳንዱ የጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ነዋሪ ከሚከተሉት አንዱን በመምረጥ ጻፍ ኮዱ ይሞላል፡፡

0 = አዳሪ ተማሪ
1 = አዳሪ ሠልጣኝ
2 = ተኚኝ ታካሚ
3 = እስረኛ
4 = ኮንትራት ሠራተኞች
5 = የጦር ኃይሎች አባል
6 = የሆቴል እንግዳ
7 = የሆቴልና የሆስቴል ነዋሪ
8 = ሌላ /ይገለጽ/

ለ. <u>ቤት የሌላቸው ነዋሪዎችን በሚመለከት</u>

በዓምድ 9 የነዋሪ ዓይነት በሚመለከት ቤት የሌላቸው ለሚለው መልስ ኮዱ ከብ በማድረግ ኮዱ በተሰጠው ካርድ ኮለም 23 ውስጥ ለተሞላላቸው የሚከተሉት ዓምዶች ወይም ክፍሎች አይሞላላቸውም፡፡

1ኛ/ ክፍል አንድ የቤት ተራ ቁጥር፣ የቤት ቁጥር፣ የቤት ንዑስ ቁጥርና የቤተሰብ ተራ ቁጥር መኖሪያ ቤት ለሌላቸው ነዋሪዎች ከ10–13 ያሉት ዓምዶች አይሞሉም፡፡

2ኛ/ በክፍል ሁለት ዓምድ 17 "ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና" በሚለው ምንም አይሞላም፡፡

3ኛ/ ክፍል ሦስት "ስለ ሞቶች መረጃ" አይሰበሰብም፡፡

4ኛ/ ክፍል አራት "ስለ መኖሪያ ቤቶች ዝርዝር መረጃ" አይሞላም፡፡

ይህ መጠይቅ በቆጠራው ቦታ የቤት የቤተሰብና የድርጅት ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ ቆጠራው ከቤት ቤት በመሄድ ስለ ቤተሰብ አባላትና ቤቶች ባሕሪያት በሚመለከት ዝርዝር መረጃ የሚሰበሰብበት ነው።

<u>የ1986 [illegible] የቤቶች ዝርዝር መጠይቅ</u>

<u>አሞላል መመሪያ</u>

መጠይቁ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የየክፍሉም አሞላል መመሪያ ከዚህ በታች ተመልክቷል።

<u>ክፍል አንድ - የአካባቢ መለያ</u>

ከዓምድ 1–13 ባሉት ዓምዶች የቆጠራው ክልል የሚገኝበት የአካባቢ መለያ መረጃ ይሞላል።

<u>ዓምድ 1 - ክፍለ ሀገር</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ክፍለ ሀገር ስም ይመዘገባል። በጥራዙ በተሰጡት ካርድ ኮሎች ኮዱ ይሰፍራል።

<u>ዓምድ 2 - አውራጃ</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት አውራጃ ስም ይመዘገባል። በጥራዙ በተሰጡት ካርድ ኮሎች ኮዱ ይሠፍራል።

<u>ዓምድ 3 - ወረዳ</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ወረዳ ስም ይመዘገባል። በጥራዙ በተሰጡት ካርድ ኮሎች ኮዱ ይሠፍራል።

<u>ዓምድ 4 እና5- ከተማና ከፍተኛ</u>

እነዚህ ዓምዶች አይሞሉም።

<u>ዓምድ 6 - የመቆጣጠሪያ ቦታ</u>

ይህ ዓምድ አይሞላም።

ዓምድ 7 — የገበሬ ማኅበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ

ቤተሰቡ የሚኖርበት የገበሬ ማኅበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ ብቻ በዓምድ 7 ከ18—20 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል::

ዓምድ 8 — የቆጠራ ቦታ

ይህ ዓምድ አይሞላም::

ዓምድ 9 — የነዋሪ ዓይነት

የነዋሪ ዓይነት መደበኛ ቤተሰብ፣ የሆቴልና የሆስቴል፣ ሌላ የጋርዮሽ ቤት ነዋሪ ወይም መኖሪያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ መጠይቅ የሚሞላለት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ የነዋሪውን ዓይነት በመለየት ከሚከተሉት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በካርድ ኮለም 23 ይሞላል::

1 = መደበኛ

2 = ሆቴልና ሆስቴል ነዋሪ

3 = ሌላ የጋርዮሽ ነዋሪ

4 = ቤት የሌላቸው

5 = ዘላን

ዓምድ 10 — የቤት ተራ ቁጥር

በቤት፣ በቤተሰብና በድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ 1 በዓምድ 9 በምዝገባው ወቅት የቤት ተራ ቁጥር ተሞልቷል:: በቅጽ 1 በዓምድ 9 የተመለከተውን የቤት ተራ ቁጥር በዓምድ 10 ከ24—26 ባሉት ካርድ ኮለሞች መገልበጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 11 — የቤት ቁጥር

በዓምድ 11 የሚሞላው የቤት ቁጥር በቤቶች፣ በቤተሰቦችና፣ በድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ በዓምድ 10 የተመዘገበውን የቤት ቁጥር በመገልበጥ ነው:: ቤቱ የቤት ቁጥር ከሌለው ዓምዱ ሠረዝ " — " ይሞላል::

ዓምድ 12 — የቤት ንዑስ ቁጥር

የቤት ንዑስ ቁጥር የሚሞላው በቤቶች፣ በቤተሰቦችና በድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ በዓምድ 11 የተመዘገበውን የቤት ንዑስ ቁጥር በመግለጥ ነው:: ቤቱ ንዑስ ቁጥር ከሌለው ዓምዱ በ ሠረዝ "—" ይሞላል::

ዓምድ 13 — የቤተሰብ ተራ ቁጥር

በቤቶች፣ በቤተሰቦችና በድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ በዓምድ 16 በቆጠራው ቦታ ውስጥ ያሉት ቤተሰቦች በተመዘገቡበት ቅደም ተከተል መሠረት በዓምድ 13 በካርዱ ኮለም 27–29 ይሞላል:: ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የሚሞላው ተራ ቁጥር በመመዝገቢያው ቅጽ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የተሰጠውን ተራ ቁጥር በመግለጥ ይሆናል:: ሆቴሎችና ሆስቴሎች እንዲሁም ሌላ የጋራ ዓሽ መኖሪያ ቤቶችና መኖሪያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች የቤተሰብ ተራ ቁጥር ስለማይኖራቸው መጠይቁ ሲሞላ ለሆቴልና ለሆስቴል እንዲሁም ለሌላ ጋራ ዓሽ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎችና ቤት ለሌላቸው ግለሰቦች በዓምድ 13 ያሉት ካርዱ ኮለሞች በሠረዝ /—/ ይሞላል::

ክፍል ሁለት — ስለቤተሰብ አባላት ዝርዝር መረጃ

ከዓምድ 14–40 ባሉት ዓምዶች ስለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ዝርዝር መረጃ ይሞላል::

ዓምድ 14 — የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር

ይህ ዓምድ በቅድሚያ ለአሥር ወይም ከዚያ ሳነሰ የቤተሰብ አባላት ለመመዝገብ እንደሚበቃ ተደርጎ ተዘጋጅቷል:: ነገር ግን የቤተሰብ አባላት ብዛት ከአሥር በላይ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ መጠይቅ መጠቀም ያስፈልጋል:: በተጨማሪው መጠይቅ ላይ በመጀመሪያ በተሞላው መጠይቅ ላይ የተሞሉት የአካባቢ መለያዎች ማለት ከዓምድ 1–13 ያሉት በሙሉ መግለጥ ይኖርባቸዋል:: እንዲሁም በተጨማሪው መጠይቅ በዓምድ 14 ከ01–10 ያሉትን ቁጥሮች በመሠረዝ በምትካቸው 11፣ 12፣...ወዘተ በሚሉት የቤተሰቡ አባላት

በሙሉ እስከተመዘገቡ ድረስ ተከታታይ ተራ ቁጥሮች በዓምድ 14 ይሰጣሉ፡፡ በጋርዮሽ የሚኖሩ ሰዎችና መኖሪያ የሌላቸው ሰዎች በሚመዘገቡበት ጊዜ እንደ አባላቱ ብዛት መጠይቆችን በመጠቀም ከላይ በተገለጸው መሠረት ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል፡፡

ዓምድ 15 — የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም

የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶችን ሙሉ ስም በዓምዱ ከመመዝገብ በፊት የቤተሰብ መደበኛ አባል፣ የቤተሰብ ኃላፊ እንዲሁም የእንግዳ ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለ ቤት፣ ቤተሰብና ድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ አሞላል በተሰጠው መመሪያ ውስጥ ዓምድ 13ን አስመልክቶ የቤተሰብ ትርጉም የተሰጠ ሲሆን የቤተሰብ ኃላፊ ትርጉም ደግሞ በዚሁ ቅጽ ለዓምድ 16 በተሰጠው ማብራርያ ተገልጿል፡፡ መደበኛ አባልና የእንግዳ ትርጉም ከዚህ በታች ተሰጥቷል፡፡

ሀ. መደበኛ የቤተሰብ አባል

አንድ ሰው መደበኛ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው፡፡ ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ የቤተሰቡ አባላት እንደ መደበኛ የቤተሰቡ አባል መቆጠር አለባቸው፡፡

የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል፡፡

1. በቆጠራው ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ቢያንስ ለስድስት ወር የኖሩ ሁሉ፣
2. የቤት ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚያድሩና ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሁሉ፣
3. በቆጠራው ጊዜ ከስድስት ወር ላነሰ ከቤተሰቡ ለጊዜው የተለዩ ለምሳሌ በእረፍት ላይ ያሉ፣ ለዓመት በዓል ወደሌላ ቦታ የሄዱ፣ ሆስፒታል የገቡ፣ ዘመድ ለመጠየቅ የሄዱና ከሥራቸው ጋር በተያያዙ ጉዳይ በጉዞ ላይ ያሉትን አባላት ሁሉ ያጠቃልላል፣
4. ሌላ መኖሪያ [illegible]

ሰ. <u>እንግዳ</u>

እንግዳ ማለት የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በተካሄደበት ኣለት የቤተሰቡ መደበኛ አባል ባይሆን እቤት ያደረ ግለሰብ ነው።

ስለዚህ ከላይ የተሰጠውን ትርጉምና ጽንሰ ሃሣብ መሠረት በማድረግ በመጀመሪያ መደበኛ የቤተሰብ አባላትን ሙሉ ስም በመጠየቅና ቀጥሎም ቤት ያደሩ እንግዶችን ሙሉ ስም በዓምድ 15 በሚከተለው ቅደም ተከተል ይመዘገባል:-

- የቤተሰብ ኃላፊ፣
- የኃላፊው ሚስት ወይም ባል፣
- ያላገቡ ልጆች በዕድሜ ቅደም ተከተል፣
- ያገቡ ልጆች ከነልጆቻቸው፣
- ሌሎች ዘመዶች፣
- ዘመድ ያልሆኑ፣
- እንግዶች፣ / የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሙሉ ከተመዘገቡ በኋላ በቤቱ እንግዶች ካደሩ እንግዶች ይመዘገባሉ/

እንግዶችን በሚመለከት በተለይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ስለ እንግዶች የሚጠየቁት የመረጃዎች ዓይነት ስም፣ የነዋሪ ሁኔታ፣ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለ ዝምድና፣ ጾታና ዕድሜ ብቻ ናቸው። እነዚህም ከዓምድ 15-19 ያሉትን ይመለከታል።

<u>ዓምድ 15.1 - ማስታወሻ</u>

በዓምድ 15 የተመዘገቡትን መደበኛ የቤተሰብ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም ለመልስ ሰጪው ማንበብና የተመዘገቡትን ብዛት በመንገር ሳይመዘገብ የቀረ መደበኛ አባል ወይም እንግዳ ካለ በዓምድ 15 መመዝገብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 16 — የነዋሪ ሁኔታ

የነዋሪ ሁኔታ ሦስት ሲሆን ከዚህ በታች ተዘርዝሯል:—

1 = በእለቱ ቤት የነበሩ ነዋሪ:— የሚባለው መደበኛ የቤተሰቡ አባል ሆኖ ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቤት የነበሩ ናቸው::

2 = በእለቱ ቤት ያልነበሩ ነዋሪ:— የቤተሰቡ መደበኛ አባል ሆኖ ቆጠራው በተ ካሄደበት እለት ቤት ያልነበሩ ናቸው::

3 = በእለቱ ቤት ያደሩ እንግዳ:— የቤተሰቡ መደበኛ አባል ባይሆን ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቆጠራው በሚካሄድበት ቤት ያደሩ ገለሰብ ናቸው::

ስለዚህ ከላይ በተሰጠው ትርጉም መሠረት የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም በዓምድ 16 በካርድ ኮለም 32 ትክክለኛው ኮድ ይሞላል::

1 = ቤት የነበሩ ነዋሪ

2 = ቤት ያልነበሩ ነዋሪ

3 = ቤት ያደሩ እንግዳ

ዓምድ 17 — ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና

በዓምድ 15 የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሚመዘገቡበት ጊዜ በመጀመሪያው መስመር የሚመዘገበው ሁልጊዜ የቤተሰቡ ኃላፊ ይሆናል:: ስለዚህ በዓምድ 17 በመ ጀመሪያው መስመር "ኃላፊ" ተብሎ ከተመዘገበ በኋላ እያንዳንዱ የቤተሰብ መደበኛ አባል ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና በተሰጠው ክፍት ቦታ ተጠይቆ ይሞላል:: ለምሳሌ ከቤተሰቡ ኃላፊ ቀጥሎ የተመዘገበችው የቤተሰቡ ኃላፊ ሚስት ከሆነች በዓምድ 17 "ሚስት" ተብሎ ይመዘገባል:: የቤተሰቡ ኃላፊ ከአንድ በላይ ሚስት ካለውና ሚስቶቹ የእሱ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና በሚሞላበት ጊዜ የመጀመሪያዋ ሚስት "የመጀመሪያ ሚስት" ሁለተኛዋን ሚስት "ሁለተኛ ሚስት"...ወዘተ እየተባለ መመዝገብ ይኖርበታል::

ልጆች ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና በሚሞላበት ጊዜ የአባታቸውና የእናታቸው ተራ ቁጥር አብሮ መጠቀስ ይኖርበታል። ለምሳሌ የኃላፊውና የሚስቱ የሆነ ወንድ/ሴት ልጅ ዝምድና በሚሞላበት ጊዜ የ01 እና የ02 ወንድ ወይም ሴት ልጅ፣ የኃላፊው ብቻ የሆነ ወንድ/ሴት ልጅ ዝምድና ሲሞላ የ01 ወንድ/ሴት ልጅ ... ወዘተ እየተባለ ይመዘገባል።

ዘመዶች በሚመለከት ይህ ዓምድ በሚከተለው ሁኔታ ይሞላል። የኃላፊው አባት፣ የኃላፊው እናት፣ የኃላፊው ወንድም ወይም የኃላፊው እህት፣ የኃላፊው የሚስት አባት፣ የኃላፊው ሚስት እናት፣ የኃላፊው ሚስት ወንድም፣ የኃላፊው ሚስት እህት...ወዘተ እየተባለ ይሞላል። ዘመድ ያልሆኑ የቤተሰቡ መደበኛ አባላትን በሚመለከት የቤት ሠራተኛ፣ አረኛ፣ ጓደኛ፣ [illegible] ወዘተ እየተባለ ይመዘገባል። የቤተሰቡ መደበኛ አባላት ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ በትክክል ከተሞላ በኋላ በዓምዱ ራስጌ ካሉት የዝምድና ኮዶች ተስማሚውን በመምረጥ በካርዱ ኮለም 33 ይሞላል። በዓምዱ ራስጌ የተዘረዘሩት የተለያዩ የዝምድና ዓይነቶችና ኮዶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል:-

0 = ኃላፊ፣
1 = የኃላፊው ሚስት ወይም ባል፣
2 = የኃላፊውና የባለቤቱ/ቷ/ ወንድ ወይም ሴት ልጅ፣
3 = የኃላፊው /ብ/ ወንድ ወይም ሴት ልጅ፣
4 = የባለቤቱ/ቷ/ ወንድ ወይም ሴት ልጅ፣
5 = የኃላፊው/የባለቤቱ እናት ወይም አባት፣
6 = የኃላፊው/የባለቤቱ ወንድም ወይም እህት፣
7 = ሌሎች ዘመዶች፣
8 = ዘመድ ያልሆኑ

## ዓምድ 18 — ጾታ

በዓምድ 15 በተመዘገቡት ግለሰቦች ስም አንጻር ጾታቸው ከተመዘገበ በኋላ በካርድ ኮለም 34 ተስማሚው ኮድ ይሞላል:: ለምሳሌ የአባሉ ጾታ ወንድ ከሆነ በስሙ አንጻር ወንድ ተብሎ ከተመዘገበ በኋላ በካርድ ኮለም "34" ኮድ "1" ይጻፋል:: እንዲሁም የአባሉ ጾታ ሴት ከሆነ በስሟ አንጻር ሴት ተጽፎ በካርድ ኮለም 34 ኮድ "2" ይሞላል:: **የአንዳንድ ሰዎች ስም ለሁለቱም ጾታዎች ሲያገለግል ስለሚችል የአባላቱን ስም ብቻ መሠረት በማድረግ ጾታቸው በግምት መሞላት የለበትም::** በአንዳንድ አካባቢ ወንዶች በሴት ስም እንዲሁም ሴቶች በወንድ ስም ስለሚጠሩ ጾታ በሚሞላበት ጊዜ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል::

## ዓምድ 19 — ዕድሜ

ዕድሜ ማለት አንድ ሰው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ቆጠራው ኣስከተካሄደበት ቀን ድረስ ያለው የጊዜ ብዛት /ቀን፣ ወር፣ ወይም ዓመት/ ነው:: ኣያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይመዘገባል:: ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው:: ለምሳሌ የአንድ ሰው ዕድሜ 15 ዓመት፣ ከ5 ወር ከ11 ቀን ቢሆን መመዝገብ ያለበት ዕድሜ 15 ዓመት ብቻ ይሆናል ኣንጂ 15 ዓመት፣ ከ5 ወር ከ11 ቀን መሆን የለበትም:: የአንድ ሕፃን ዕድሜ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ በዓምድ 19 በካርድ ኮለም 35—36 ባለው ቦታ "00" ይመዘገባል:: እንዲሁም የአንድ ሰው ዕድሜው 98 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ "98" ብቻ በካርድ ኮለም 35 ኣና 36 ይመዘገባል::

ዕድሜአቸውን በትክክል የማያውቁ ወይም ዕድሜአቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች ኣንደሚያጋጥሙ ይገመታል:: ስለዚህ የኣያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ በተቻለ መጠን ለማግኘት ያለመሰልቸት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል:: ኣነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱትን ማጤን ይገባል::

ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌሳው አባል በመዛመድ በተቻለ መጠን ትኮኮለኛ የሆነውን ገመቶ መጻፍ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም አንድ አባል ብገባበት ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደነበረ፣ በጋብቻ ስንት ዓመት እንደቆዩና እንዲሁም ከልጆቹ ዕድሜ ጋር በማዛመድ ዕድሜውን ለመገመት ይቻላል።

አንዳንድ ሰዎች ዕድሜአቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም የቀናቸዋል። ስለዚህ ዕድሜአቸውን መግለጽ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትኮኮለኛውን ዕድሜ ለማግኘት መሞከር ያስፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች በኣርገጥ ዕድሜአቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣...ወዘተ ሊሆን ይችላል።

በተለይ ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት ያላለፈ ሕፃናት ልጆች የተወለዱበትን ጊዜ ወላጆች ሊያስታውሱት ስለሚችሉ የሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ዕድሜ በሙሉ ዓመት በትኮኮል መጻፍ አለበት። አልፎ አልፎ የሕፃናትን ትኮኮለኛ ዕድሜ ለማግኘት ቀላል የማይሆንበት ሁኔታ ካጋጠመ ከፍተኛ ጥረት አድርጉ ትኮኮለኛውን ዕድሜ በማወቅ በትኮኮል መጻፍ ይኖርበታል።

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ትኮኮለኛውን ዕድሜ ለማግኘት በቂ ጥረት አድርጉ ትኮኮለኛ መልሶችን ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎችን በመቅረብና በማስላት የእያንዳንዱ አባል ትኮኮለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት በዓምድ 19 ውስጥ በከርዱ ክፍሎች 35–36 ይጻፋል።

ዓምድ 20 — ኃይማኖት፣ የ....... ኃይማኖት ተከታይ ነው?

ኃይማኖት አንድ ግለሰብ የሚከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅቶች አባልነት ነው። የኃይማኖትን ዓይነት የሚመለከት ጥያቄ ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ በማቅረብ ይህን ዓምድ መሙላት ያስፈልጋል። ኃይማኖት በሚጠየቅበት

ጊዜ ክርስቲያን የሚል መልስ ከተገኘ ዓምድ 20 ከኮድ 1—3 የተሰጧቸው ውስጥ የትኛው መሆኑን አጣርቶ ይሞላል፡፡ ስለዚህ በዓምዱ በተሰጠው ባዶ ቦታ የእያንዳንዱ አባል የሚከተለውን የኃይማኖት ዓይነት በመጠየቅ በዓምዱ ራስጌ በተመለከተውና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የኃይማኖት ዓይነቶች መሠረት በማድረግ የግለሰቡ የኃይማኖት ዓይነት ተመዝግቦ በካርዱ ኮለም 37 ትክክለኛው ኮዱ ይሞላል፡፡

1 = ኦርቶዶክስ /ተዋህዶ/

2 = ፕሮቴስታንት /ሰባት ቀን አድቬንቲስት፣ ጴንጤቆስጤና፣ ሉተራያን መካነ የሱስ፣ ባፕቲስት፣ መነናይት፣ አንጀሊካን፣ ፕረስቢተርያን ...../

3.= ካቶሊክ፣

4 = እስላም

5 = ሌላ ኃይማኖት /ለምሳሌ — ሂንዱ፣ ይሁዳ፣ ጆሆባ፣ ቡሃይ፣... ወዘተ/

6 = ባዕድ አምላክ /በፀሐይ፣ በወንዝ፣ በዛፍ...ወዘተ/

7 = ኃይማኖት የሌለው /ምንም ዓይነት ኃይማኖት የማይከተል/

አንዳንድ ጊዜ የቤተሰቡን ኃላፊ ኃይማኖት በመውሰድ የሌሎችን የቤተሰቡን አባላት ኃይማኖት ለመገመት ይሞከር ይሆናል፡፡ ይህ ትክክል ሲሆን ስለማይችል የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ኃይማኖት በመጠየቅ የተገኘው ኃይማኖት ዓይነት በዓምዱ ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 37 ትክክለኛው ኮዱ መሞላት አለበት፡፡ ባለና ሚስት የተለያዩ ኃይማኖት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

ለሕፃናት የሚሞላው የኃይማኖት ዓይነት ወላጆቻቸው የሚከተሉት ኃይማኖት ይሆናል፡፡ የተለያዩ ኃይማኖት ከሚከተሉ ወላጆች ለተወለደ ሕፃን የአባቱን ኃይማኖት በመውሰድ በዓምዱ ይሞላል፡፡

1. አፉን ያልፈታ ሕፃን ቋንቋን በሚመለከት ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ በቤት የሚጠቀሙበት ቋንቋ በዓምዱ ይሞላል።

2. መናገር ለተሳናቸው ግለሰቦች ቤተሰቡ አብዛኛውን ጊዜ በቤት የሚጠቀምበት ቋንቋ በዓምዱ ይመዘገባል።

3. አንድ ግለሰብ ብቻ በሚኖርበት ቤተሰብ አብዛኛውን ጊዜ በቤት የሚጠቀምበት ቋንቋ ስለማይኖር ለዚህ ግለሰብ በሚኖርበት አካባቢ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀምበት ቋንቋ በዓምዱ ይመዘገባል።

4. የውጭ አገር ቋንቋ የሚጠቀሙ የቤተሰብ አባላት ካጋጠሙ በዓምዱ የውጭ አገር ቋንቋው ስም ይሞላል።

<u>ዓምድ 23 – 26 የትውልድ ቦታ</u>

የአንድ ግለሰብ የትውልድ ቦታ ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ እናቱ ትኖርበት የነበረው መደበኛ የመኖሪያ ቦታ ሲሆን በከተማ ትኖር ከነበረ ትኖርበት የነበረ ከተማ፣ ገጠር ትኖር ከነበረ ደግሞ ትኖርበት የነበረ ወረዳ ነው። የትውልድ ቦታ በሚመዘገብበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ አንድ ሰው በሆስፒታል ወይንም በሌላ ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ ወይም ከተማ ወይም በእናቱ ወላጆች መኖሪያ ቢወለድ የግለሰቡ የትውልድ ቦታ ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ እናትየው ትኖርበት የነበረ መደበኛ መኖሪያ ይሆናል እንጂ ግለሰቡ የተወለደበት ሆስፒታል የሚገኝበት ከተማ፣ ወረዳ፣ አውራጃ ወይም ክፍለ ሀገር አይሆንም። ነገር ግን እናቱ ልጁ ከተወለደ በኋላ በተወለደበት ቦታ ማለት በሆስፒታል፣ በእናቱ

ወላጆች መኖሪያ፣....ወዘተ ከስድስት ወር በላይ ከቆዩ የሕፃኑ የትውልድ ቦታ ሆስፒታሉ የሚገኝበት ከተማ ወይም የልጁ እናት ወላጆች የሚኖሩበት ከተማ ወይም ወረዳ ይሆናል። ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል የትውልድ ቦታ በሚከተለው መሠረት በዓምዱ በተሰጠው ቦታ ይሞላል።

የትውልድ ቦታ የሚለው ጥያቄ አራት ዓምዶችን የያዘ ሲሆን እነርሱም፣

ዓምድ 23 — ከተማ

ዓምድ 24 — ወረዳ

ዓምድ 25 — አውራጃ

ዓምድ 26 — ክፍለ ሀገር

1. የአንድ በገጠር የተወለደ የቤተሰብ አባል የትውልድ ቦታ ቆጠራ በሚካሄድበት ወረዳ ከሆነ ግለሰቡ በዚሁ ወረዳ የተወለደ መሆኑን ለመግለጽ ከ24–26 ባሉት ዓምዶች በተሰጡት ክፍት ቦታዎች "እዚሁ የሚል ቃል ይመዘገባል። ከዚያም በካርድ ኮለም 42–49 ሥር ባሉት ሣጥኖች "××፣ ××፣ ××፣" ይሞላል። ለምሳሌ የሕዝብ ቆጠራው የሚካሄደው በአዋባ ዙሪያ ወረዳ ከሆነና የቤተሰቡ አባል አዋባ ዙሪያ ወረዳ የተወለደ ከሆነ የዚህ ግለሰብ የትውልድ ቦታ እዚሁ ወረዳ ስለሆነ ከ24–26 ባሉት ዓምዶች "እዚሁ" የሚል ቃል ተመዝግቦ 44–49 ባሉት ካርድ ኮለሞች ሥር የሚገኙት ሣጥኖች "××፣ ××፣ ××፣" ይሞላሉ።

2. የአንድ ቤተሰብ አባል የትውልድ ቦታ ቆጠራው ከሚካሄድበት ወረዳ ውጭ በሌላ ከተማ ከሆነ፣ የግለሰቡን የትውልድ ቦታ ለመግለጽ በዓምድ 23 ግለሰቡ የተወለደበት ከተማ ስም ይመዘገባል። በዓምድ 24 ደግሞ ግለሰቡ የተወለደበት ከተማ የሚገኝበት ወረዳ ስም ይሞላል። እንዲሁም በዓምድ 25 እና 26 ግለሰቡ የተወለደበት ከተማ የሚገኝበት አውራጃና ክፍለ ሀገር ስም በተከታታይ ይመዘገባል። ነገር ግን ከ42–49 ባሉት ካርድ ኮለሞች ሥር በሚገኙት ሣጥኖች ውስጥ ምንም አይሞላም።

× = ከስድት ፩ምረው ያለማቋረጥ እስከ ቀጠራው ቀን ድረስ በከተማው ለሚኖሩና አዲስ ለተወለዱ ሕፃናት

0 = ከዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

1 = አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

2 = ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሦስት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ

3 = ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከአራት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለሆሩ፣

4 = አራት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከአምስት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

5 = አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከስድስት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

6 = ከስድስት እስከ 9 ዓመት ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

7 = ከአሥር እስከ 15 ዓመት ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

8 = ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

ዓምድ 28 የአካል ስንኩልነት ሁኔታ፣....አካለ ስንኩል ናቸው? ከሆኑ ዓይነቱ ይገለጽ

ሲወለድ ወይም ከተወለደ በኋላ የበሽታ፣ የአእምሮ፣ ወይም የሌላ የአካል ክፍል መበላሸት የደረሰበት ግለሰብ አካለ ስንኩል ይባላል:: በአጠቃላይ አካለ ስንኩል የሚባለው ግለሰቡ የአካሉ ክፍል በመሰናከሉ፣ በመጉዳቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት ሌሎች ደህና የሆኑ ሊያከናውኑት የሚችሉትን ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን ባለመቻሉ የበሽታና የኢኮኖሚ ተግባራትን አሟልቶ በማከናወን ረገድ የተጓጎለ ነው:: ስለዚህ እያንዳንዱን የቤተሰብ መጠይቅ አባል ስለአካለ ስንኩልነት ሁኔታ በመጠየቅ በዓምድ 28 ይመዝገባል::

አንዳንድ ግለሰቦች አካለ ስንኩል ነዎት ወይ? ተብለው ቢጠየቁ ያስ ስለማ ይሳቸው ይህንን ጥያቄ ለመለስ በጨዎች ሲያቀርቡ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ይኸውም አካለ ስንኩል ነዎት ወይ? ብሎ በመጠየቅ ፈንታ የጤና ጉድለት አለብዎት ወይ? ብሎ በመጠየቅ አግባብነት ዐይንዎ የማየት፣ ጆሮዎ የመስማት፣ እግርዎ፣ እጅዎ፣ ...ወዘተ ችግር አለብዎት ወይ? ብሎ በመጠየቅ የአካል ጉድለት ካለባቸው በዘወርዋራ መንገድ ጠይቆ ሁኔታውን ማወቅ ያስፈልጋል።

አንድ ግለሰብ ከአንድ የበለጠ የአካል ስንኩልነት ሁኔታ ሊኖረው ይችላል። እንደየሁኔታው የእያንዳንዱን የቤተሰብ መደበኛ አባል የአካለ ስንኩልነት ሁኔታ በመጠየቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የአካለ ስንኩልነት ዓይነቶች ከኮድ 00→27 የተዘረዘሩትን መሠረት በማድረግ ግለሰቡ ያለበትን የአካል ስንኩልነት ሁኔታ በተሰጠው ባዶ ቦታ በመጻፍ ኮዱንም በካርድ ኮለሞች 51 እና 52 መመዝገብ ያስፈልጋል።

## የአካለ ስንኩልነት ሁኔታ ዓይነት ኮድ ዝርዝር

| ኮድ | | የአካለ ስንኩል ሁኔታ ዓይነት |
|---|---|---|
| 00 | = | አካለ ስንኩል ያልሆነ፣ |
| 01 | = | ሁለቱም ዐይን የጠፋ /ሙሉ በሙሉ የታወረ/፣ |
| 02 | = | አንድ ዐይን ብቻ የጠፋ /በግማሽ የታወረ/፣ |
| 03 | = | ሁለቱም ጆሮ የማይሰማ /ሙሉ በሙሉ የደነቆረ/፣ |
| 04 | = | አንድ ጆሮ ብቻ የማይሰማ /በግማሽ የደነቆረ/፣ |
| 05 | = | ደንቆሮና ዲዳ፣ |
| 06 | = | ደንቆሮ፣ ዱዳና እውር፣ |
| 07 | = | አንድ እግሩ ከጉልበት በታች የተቆረጠ፣ |
| 08 | = | አንድ እግሩ ከጉልበት በላይ የተቆረጠ፣ |
| 09 | = | ሁለት እግሩ ከጉልበት በታች የተቆረጠ፣ |

ኮድ      የአካል ስንኩል ሁኔታ ዓይነት

10 = ሁለት ኣግሩ ከጉልበት በላይ የተቆረጠ።

11 = ኣጁና ኣግሩ የተቆረጠ።

12 = አንድ ኣጅ ከክርኑ በታች የተቆረጠ።

13 = አንድ ኣጅ ከክርኑ በላይ የተቆረጠ።

14 = ሁለት ኣጅ ከክርኑ በታች የተቆረጠ።

15 = ሁለት ኣጅ ከክርኑ በላይ የተቆረጠ።

16 = አንካሳ /አንድ ኣግር ብቻ/።

17 = አንካሳ /ሁለቱም አግሮች/።

18 = የአእምሮ ሕመም /እብደት/።

19 = ሽባ /አንድ ኣግር ብቻ/።

20 = ሽባ /ሁለቱም አግሮች/።

21 = ሽባ /አንድ ኣጅ ብቻ/።

22 = ሽባ /ሁለቱም ኣጆች/።

23 = ሙሉ በሙሉ ሽባ /ሁለቱም ኣግሮችና ሁለቱም ኣጆች/።

24 = አንድ ኣጁና አንድ ኣግር ሽባ።

25 = ቁምጥና።

26 = የሚጥል በሽታ።

27 = ብዙ የአካል ስንኩልነት

28 = ሌላ /ይገለጽ/

**ዓምድ 29—30 የትምህርት ሁኔታ፤ /ዕድሜያቸው አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚጠየቅ/**

በዓምድ 29 ዕድሜው አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ ትምህርት ቤት ገብቶ በመማር ላይ ከሆነ የሚማርበትን የክፍል ደረጃ፤ አሁን በመማር ላይ ካልሆነ ከዚህ በፊት ትምህርት ቤት ገብቶ ተምሮ የሚያውቅ ወይም የማያውቅ መሆኑን የሚያመለክቱ መረጃዎች ይሞላሉ፡፡ እንዲሁም በዓምድ 30 የቤተሰብ አባል ማንበብና መጻፍ የሚችል መሆኑና አሁን ትምህርት ቤት ገብቶ በመማር ላይ ቢሆንም ባይሆንም የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ደረጃን በሚመለከት መረጃዎች ይሞላሉ፡፡

**ዓምድ 29 ትምህርት ቤት የመማር ሁኔታ**

**አሁን በትምህርት ቤት በመማር ላይ ካሉ የሚማሩበት ክፍል፤ ከዚህ በፊት ከተማሩ ኮድ "24" እንዲሁም ተምረው የማያውቁ ከሆነ ኮድ"25" ይሞላል፤**

ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ በቆጠራው ጊዜ በትምህርት ቤት በመማር ላይ መሆናቸውና የሚማሩበት የክፍል ደረጃ በዓምዱ ይሞላል፡፡ በመማር ላይ ሳልሆኑ፡—

ሀ. ከዚህ በፊት በትምህርት ቤት የተማሩ፡ ስለመሆናቸው ወይም

ለ. ፈጽሞ በትምህርት ቤት ገብተው ተምረው የማያውቁ ስለመሆናቸው ለቤተሰብ ኃላፊዎች ወይም ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ትክክለኛ መልስ ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎች በመቅረብና በማጣራት በትምህርት ላይ ላሉት ቀጥሎ ከተሰጠው ኮድ ዝርዝር በዓምድ 29 በኩርዱ ከገጽ 53 እና 54 ትክክለኛው ኮድ ይሞላል፡፡ ኮዱ የሚሞላው የተገኘውን መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በአግባቡ ከተጻፈ በኋላ ነው፡፡

## የሚማሩበት ክፍል ደረጃ

### ሀ. በመማር ላይ ያሉ

00 = ቅድመ ትምህርት ቤት ወለት በመለማመጃ ወይም ከአንደኛ ክፍል በታች ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

01 = በአንደኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

02 = በሁለተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

03 = በሦስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

04 = በአራተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

05 = በአምስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

06 = በስድስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

07 = በሰባተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

08 = በስምንተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

09 = በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

10 = በአሥረኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

11 = በአሥራ አንደኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

12 = በአሥራ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

20 = ከ12ኛ ክፍል በላይ በሆነ ት/ቤት ተቋም፣ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ቢ.ኤስ.ሲ/ የሚያስገኝ ትምህርት በመከታተል ላይ ያሉ ሁሉ፣

21 = ከ12ኛ ክፍል በላይ በዩኒቨርሲቲ ወይም በኮሌጅ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ የሚያስገኝ ትምህርት በመከታተል ላይ ያሉ ሁሉ፣

22 = በዩኒቨርሲቲ በድሕረ ምረቃ ፕሮግራም በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

23 = በመደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጐሙ በማይችል የትምህርት መስጫ ድርጅት ትምህርት በመከታተል ላይ ሳሉ ለምሳሌ በቄስና በቁራን ትምህርት ቤት፣ በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሁሉ፣ አነስተኛ የትምህርት ዝግጅት የማይጠይቁ የሙሠለጠኛ ተቋሞች፣

ሰ. <u>ትምህርት ለተከታተሉና በቆጠራው ጊዜ በመማር ላይ ያልሆኑ፣</u>

24 = ከዚህ በፊት በትምህርት ቤት፣ ተቋም፣ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ለተከታተሉ ግን በቆጠራው ጊዜ በመማር ላይ ሳልሆኑ ሁሉ፣

ሸ. <u>ትምህርት ተከታትለው ለማያውቁ፣</u>

25 = ከዚህ በፊት በማንኛውም ት/ቤት፣ ተቋሞች፣...ወዘተ ትምህርት ተከታትለው ለማያውቁና በቆጠራው ጊዜም በመማር ላይ ሳልሆኑ ሁሉ፣

አንዳንድ ሙሉ በሙሉ ቀጥታ በሆነ መንገድ መልስ ሊገኝላቸው የማይችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ የሚከተለው ምሳሌ የመረጃ አሰባሰቡን ሁኔታ በይበልጥ ገልጾ ያደርገዋል።

በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት የአንደኛ ዓመት ትምህርቱን አጠናቅቆ የሁለተኛ ዓመትን ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኝ የሚማርበት የኮፍል ደረጃ ስንተኛ ነው? ይህ የሚገኘው ወደ ትምህርት ቤቱ ለመግባት በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ማጠናቀቅ ያለበት የኮፍል ደረጃ አሁን ከደረሰበት የትምህርት ዓመት በመደመር ይሆናል። ይኸውም ወደ ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚቻለው ቢያንስ የ10ኛ ኮፍል ትምህርት በማጠናቀቅ ስለሆነ አሁን የሚማርበት የኮፍል ደረጃ 12 /10+2/ መሆን አለበት።

01 = የአንደኛ ክፍል ትምህርትን ሳጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ

02 = የ2ኛ ክፍል ትምህርትን ሳጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ፣ በመሠረተ ትምህርት በሚሰጣቸው ትምህርት ማንበብና መጻፍ ችለው በሌላ ቦታ ትምህርት ያላቀጠሉ የሁለተኛ ክፍል ትምህርት እንዳጠናቀቁ ይቆጠራሉ፣

03 = የ3ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁና መንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ

04 = የ4ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

05 = የ5ኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ

06 = የ6ኛ " " " "

07 = የ7ኛ " " " "

08 = የ8ኛ " " " "

09 = የ9ኛ " " " "

10 = የ10ኛ " " " "

11 = የ11ኛ " " " "

12 = የ12ኛ " " " "

20 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ ለመስገኘት ባልታቀደ የትምህርት ፕሮግራም ቢሆን ቢኤ፣ ቢኤ፡ በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ የውስጥ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ሳጠናቀቁ ሁሉ፡፡

21 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ቢ/ ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ሳጠናቀቁ ገን ዲግሪ ሳስገኙ ሁሉ፡፡

22 = የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ኤል.ኤል.ቢ/ ያገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሁሉ፡፡

23 = በዩኒቨርሲቲ በድሕረ ምረቃ ፕሮግራም /ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ/ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን የኤም.ኤ፣ ኤም.ኤስ.ሲ ወይም ኤል.ኤል.ኤም/ ዲግሪ ያላገኙ ሁሉ፡፡

24 = የኤም.ኤ፣ የኤም.ኤስ.ሲ፣ ወይም የኤል.ኤል.ኤም /ማስትሬት/ ዲግሪ ያገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሁሉ፡፡

25 = የዶክትሬት ዲግሪ ያገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ፡፡

26 = ማንበብና መጻፍ በሚገባ የሚችሉ ሆነው ግን ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሲተረጎም ለማይችሉ ሁሉ፣ ለምሳሌ በገዳሞችና በመሳሰሉት የቄስ ትምህርት ቤቶች፣ በቁራን ትምህርት ቤቶች ብቻ ትምህርት ተከታትለው ማንበብና መጻፍ የቻሉ ቄሶች፣ ደብተራዎች፣ መነኩሳት፣ ሼኮች፣ ... ወዘተ የደረሱት የትምህርት ደረጃ እዚህ ይመደባል፡፡ እንደዚሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን እርዳታ እየጠየቁ በመማርና አንደኛ ኮርስ ከመጨረሳቸው በፊት ማንበብና መጻፍ በሚገባ የቻሉ ሁሉ የትምህርት ደረጃቸው እዚህ ይመደባል፡፡ መሠረተ ትምህርት እየተማሩ ማንበብና መጻፍ የሚችሉትንም ያጠቃልላል፡፡

3 = የተፋቱ /ከቆጠራው ቀን በፊት ባል ወይም ሚስት አግብቶ ወይም አግብታ የነበረ ነገር ግን ከቆጠራው ቀን በፊት በሕጋዊ ወይም በባሕላዊ መንገድ የተፋታ ወይም የተፋታች/

4 = ባል የሞተባት ወይም ሚስት የሞተችበት /ባል /ሚስት ከሞተባቸው በኋላ እስከ ቆጠራው ቀን ያላገቡ/

5 = የተለያዩ /ጋብቻቸው በሕግ ወይም በባሕል መሠረት ያላፈረሰ ነገር ግን ባለመግባባት የተነሳ በቆጠራው ቀን ተለያይተው ያሉ ባልና ሚስት/

ስለዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የጋብቻ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰቡ አባላት በዓምድ 31 በካርድ ኮለም 57 የጋብቻ ሁኔታ የሚያመለክተው ትኮድ ይሞላል፡፡

ዓምድ 32—46 አሥር ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባላት የሚቀርቡ የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚመለከቱ ጥያቄዎች

ስለኢኮኖሚ ሁኔታዎች በገጠር የሚሰበሰቡ መረጃዎች ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት ባለፉት 12 ወራት የሚመለከቱ መደበኛ የኢኮኖሚ ተግባሮችን ነው፡፡ ይኸውም ባለፉት 12 ወራት ግለሰቦች አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ መሥራታቸው፣ ምርታማ ሥራ ካልሠሩ ያልሠሩበት ምክንያት፣ የሥራ ዓይነት፣ የድርጅቱ ዋና ምርት፣ ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎት ወይም የድርጅቱ የንግድ ዓይነት እንዲሁም የቅጥር ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎች ይሰበሰባሉ፡፡

ዓምድ 32 — ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ሠርተዋል?

ዕድሜው አሥር ዓመትና በላይ ለሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት ባለፉት 12 ወራት ምርታማ ሥራ መሥራቱን በመጠየቅ መልሱ ሠራሁ ከሆነ ኮድ "1" መልሱ አልሠራም ከሆነ ኮድ "2" በዓምድ 32 በካርድ ኮለም 58 ይሞላል፡፡

መ. የኤሌክትሪክ ኃይል ጋዝና ውኃ፣ እነዚህን የማመንጨትና የማሰራጨት ተግባርን ያጠቃልል::

ሠ. ኮንስትራክሽን /ሕንፃ ሥራ/፣ ሕንፃዎችን፣ መንገዶችን፣ ድልድዮችና እንደ ግድብ የመሳሰሉትን የመሥራት ተግባርን ያጠቃልላል::

ረ. ንግድ፣ የሸቀጣ ሸቀጦችንና የዕቃዎችን ቅርጽና ይዘት ሳይለውጥ ገዝቶ የመሸጥ ተግባርን ያጠቃልላል:: ለምሳሌ ጠርቃ ጠርቅ ንግድ፣ ሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ፣...ወዘተ ያጠቃልላል:: ጠላ፣ ጠጅ፣ ካቲካላ የመሳሰሉትን በቤት አምርቶ መሸጥም በዚህ ይጠቃለላል:: የጅምላና የችርቻሮ ንግድም በዚሁ ያጠቃልላል::

ሰ. ትራንስፖርትና መገናኛ፣ ይህም ከቦታ ቦታ መንገደኞችን፣ ዕቃዎችንና ሸቀጣ ሸቀጦችን ለግለሰብ፣ ለቤተሰብና ለድርጅት የማጓጓዝ አገልግሎት የመስጠት ተግባርን የፖስታ፣ የቴሌፎን፣ የቴሌግራፍና የቴሌክስ አገልግሎትን የመሳሰሉትን የመስጠት ተግባርን ያጠቃልላል::

ሸ. የፋይናንስ ሥራ፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስና የኦዲቲንግ ድርጅቶች የሚሰጡት የገንዘብና የመድን አገልግሎት ያጠቃልላል::

ቀ. ሌሎች አገልግሎቶች፣ ከመጓጓዣ አገልግሎት ሌላ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ለግለሰብ፣ ለቤተሰብና ለድርጅት የመሸጥ ተግባር ነው:: ለምሳሌ የሕክምና አገልግሎት፣ የትምህርት አገልግሎት፣ የአገር አስተዳደር ወይም የመከላከያ አገልግሎት፣ የቤት አድራጎትና የሃይማኖት አገልግሎት፣ ግላዊ አገልግሎት /የፀጉር መሥራት፣ ለገንዘብ ከፍያ ልብስ ማጠብና መተኮስ/፣ መሣሪያዎች መጠገንና ሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል:: የጋራዥ አገልግሎት፣ ጠርቅ ቀርበሳቸው ልብስ የሚሰፉ...ወዘተ በዚህ ይጠቃለላሉ::

06 = <u>አካለ ስንኩል፡</u> እነዚህ ግለሰቦች በሰውነት መጉደል ወይም በአእምሮ መታወክ ምክንያት ሥራ ለመሥራት ያልቻሉ ናቸው። አካለ ስንኩል ሆነው በለመና ከተዳደሩ በለማኞች ይመደባሉ።

07 = <u>ለማኞች፡</u> እነዚህ ግለሰቦች በልመና የሚተዳደሩ ናቸው። አካለ ስንኩል ሆነው ከለመኑ እንደ ለማኞች ይቆጠራሉ።

08 = <u>ቤትና አዳሪዎች፡</u> በቤትና አዳሪነት የሚተዳደሩ እንደ ቡና ቤት አሻሻጭ፣ መጠጥ ደርድረው ወይም ባይደረድሩ በዚህ ተግባር የሚተዳደሩና የመባሰሉት ናቸው።

09 = <u>ልጅ፡</u> ዕድሜው ለሥራ ያልደረሰ በመሆኑ ያልሠራና በመማርም ላይ ያልሆነ ነው።

10 = <u>በጡረታ፣ በቤተሰብ እርዳታና መዋጮ የሚተዳደሩ፣</u> እነዚህ ግለሰቦች በቤት አበል፣ በጡረታ፣ እራሱ ባጠራቀመው ገንዘብ፣ በቤተሰብ እርዳታና መዋጮ የሚተዳደሩ ናቸው። ያረጁ ተጧሪዎችም በዚህ ይመደባሉ። ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ካጋጠመም በዚህ ይመደባሉ።

ቀደም ብሎ የተጠቀሱትን የኮዶች ዝርዝር መሠረት በመደረግ የተገኘውን መልስ በዓምድ 33 በተሰጠው ቦታ በአጭር በመጻፍ በካርዱ ኮለሞች 59 እና 60 ኮድ ይሞላል።

<u>ማሳሰቢያ፡</u>

1. አንድ ግለሰብ ምንም እንኳ አካለ ስንኩል [illegible] ቢሆንም በዓምድ 32 የተሰጠውን "የመደበኛ ሥራን" ትርጉም የሚያሟላ ሥራ ከሠራ ሥራ እንደሠራ ይቆጠራል እንጂ ሥራ ያላሠራበት ምክንያት በኮድ "06" አካለ ስንኩል ተብሎ አይሞላበትም።

2. አንድ ግለሰብ ምንም እንኳን ከጡረታ፣ ከኢንሹራንስ፣ ከንብረት፣...ወዘተ. ገቢ አያለው ባለፈት 12 ወራት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ከሠራ እንደሠራ ይቆጠራል እንጂ በጡረታ በቤተሰብ እርዳታና መጥ እንደሚተዳደር አይቆጠርም፡፡

3. የማታ ተማሪዎች ሆነው ቀን ምንም ሥራ የሌላቸው ነገር ግን ሥራ ለማግኘት ጥረት ያደረጉ "ሥራ አጥ" ተብለው እንደሁኑታው ይመዘገባሉ፡፡

<u>ዓምድ 34 — 36 ባለፈት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ለሠሩ፣ የሥራ ልምድ ያለቸው ሥራ አጥ /በዓምድ 33 ኮድ 02/፣ ሥራ ኖሮአቸው ባለፈት 12 ወራት ያልሠሩ /በዓምድ 33 ኮድ 03/ የሚጠየቁ፡፡</u>

<u>ዓምድ 34 — ሥራቸው ምንድን ነው?</u>

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁት ከቆጠራው ቀን በፊት ባሉት 12 ወራት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ለሠሩ፣ የሥራ ልምድ ላላቸው ሥራ አጦ፣ ሥራ ኖሮአቸው ባለፈት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ላልሠሩ ግለሰቦች ብቻ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች አንድ የተለየ ሥራ ይኖራቸዋል፡፡ ይህ የሥራ ዓይነት በዚህ ዓምድ ይመዘገባል፡፡ ይህ የሥራ ዓይነት በሚመዘገብበት ጊዜ የሥራውን ዓይነት ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል አኳኋን መመዝገብ አለበት፡፡ ለምሳሌ "የሕክምና ሠራተኛ" ብሎ መመዝገብ የሥራውን ዓይነት ለይቶ አይገልጻም፡፡ ስለዚህ የግለሰቡን የሥራ ዓይነት በመለየት "የጤና ረዳት" ሲኒቴሪያን" "ነርስ" ወይም የሕክምና ዶክተር መሆኑን መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በታች ለአንዳንድ የሥራ ዓይነቶች ዝርዝር ቀርቧል፡፡

- ቀማሚ ሒሳብ
- ኢንጂነር
- የሕክምና ዶክተር
- የጥርስ ሐኪም
- ፖስተኛ
- የኢንሹራንስ የሽያጭ ክፍል ሠራተኛ
- አባላፊ
- ፀጉር አስተካካይ

- ፋርማሲስት
- ነርስ
- ጠበቃ
- ዳኛ
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አስተማሪ
- የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ
- ደራሲ
- ላይብሬሪያን
- ልብስ ሰፊ
- ብረታ ብረት ሠራተኛ
- ጠላ ነጋዴ
- አናጢ
- መዝገብ ያዥ
- ታይፒስት
- የግምጃ ቤት ፀሐፊ
- የፀጉር ሠራተኛ /ፃሲት/
- ሸማኔ
- ጫማ ሠሪ
- የቧንቧ ሠራተኛ
- ሹፌር
- የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ሠራተኛ
- የባንክ ቤት ገንዘብ ተቀባይ /ከፋይ/
- ፀሐፊ
- አራሽ ገበሬ /እህል፣ቡና፣አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ጥጥ፣...ወዘተ/
- ከብት አርቢ/የሚያመርቱትን ያጠቃልላል/
- እረኛ
- ዓሣ አጥማጅ
- ከሰል አክባይ

አንዳንድ ግለሰቦች ከአንድ የበለጠ ሥራ ሊኖራቸው ይችላል:: በዚህ ጊዜ በዓምድ 34 መመዝገብ ያለበት የሥራ ዓይነት ግለሰቡ ከሁለቱ ወይም ከሦስቱ ሥራዎች ውስጥ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ይበልጡን ጊዜ ያጠፋበት የሥራ ዓይነት ነው::

በሚመለከተው ቤተሰብ ስም አንጻር የሥራው ዓይነት ይመዘገባል እንጂ ከ61–62 ባሉት ካርድ ኮለሞች ምንም አይሞላም::

<u>ዓምድ 35 የሚሠራበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምንድን ነው?</u>

ዓምድ 35 ለመሙላት ግለሰቡ የት ወይም በየትኛው ድርጅት እንደሚሠራ በመጠየቅና ከዚያም ድርጅቱ ምን እንደሚያመርት፣ እንደሚነግድ /የጅምላ ወይም የችርቻሮ ንግድ/ ወይም ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ መጠየቅ ያስፈልጋል:: በዚህ

ዓምድ የምርቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የንግዱ ዓይነት ግልጽ በሆነ መንገድ መመዝገብ ይኖርበታል።

ከዚህ ቀጥሎ አንዳንድ የምርት፣ የንግድ ወይም አገልግሎት ዓይነቶች ተዘርዝረዋልና እነዚህን መረዳት ያስፈልጋል።

1. ግብርና፣ አደንና ዓሣ

ሀ. የእህል ጥራጥሬ እርሻ
ለ. አትክልትና ፍራፍሬ እርሻ
ሐ. እንሰት እርሻ
መ. ቡና እርሻ
ሠ. ጫት እርሻ
ረ. ከብት እርባታ
ሰ. ዶሮ እርባታ
ሸ. እአደን
ቀ. ዓሣ ማስገር...ወዘተ

2. ማዕድን፣ ድንጋይና አሸዋ ማውጣት

ሀ. ድንጋይ ማውጣት
ለ. ጨው ማውጣት
ሐ. ወርቅ ማውጣት
መ. አሸዋ ማውጣት...ወዘተ

3. ማኑፋክቸሪንግ /ማምረቻ/

ሀ. ቄራዎች
ለ. ወተትና የወተት ውጤት በፋብሪካ ማዘጋጀት
ሐ. የምግብ ዘይት ማምረት
መ. ስኳር ማምረት
ሠ. ጨርቃ ጨርቅ ማምረት
ረ. ጠላ፣ ጠጅ ወይም ካቲካላ ጠምቆ ለሌላ ነጋዴ መሸጥ ...ወዘተ

4. ኤሌክትሪክ ጋዝና ውሃ

ሀ. ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል
ለ. የውሃ ሥራዎችና የውሃ እደላ

5. ኮንስትራክሽን

ሀ. የሕንፃ ሥራ ተቋራጭ
ለ. የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ
ሐ. የሕንፃ ጥገና...ወዘተ

6. ንግድ፣ ሆቴል፣ ሬስቶራንት፣ቡና ቤት፣ ቁርስ ቤት፣...ወዘተ

ሀ. የውጭ ንግድ
ለ. የገቢ ንግድ
ሐ. የችርቻሮ ንግድ
መ. የአገር ውስጥ ጅምላ ንግድ

ሠ. ሆቴል

ረ. ሬስቶራንት...ወዘተ

7. <u>ትራንስፖርትና መገናኛ</u>

ሀ. የመንገድ ትራንስፖርት

ለ. የባሕር ትራንስፖርት

ሐ. መገናኛ...ወዘተ

8. <u>ፋይናንስ፣ ኢንሹራንስና የንግድ አገል.</u>

ሀ. ባንክ

ለ. ኢንሹራንስ

ሐ. የሕግ አገልግሎት

መ. የሂሣብና ኦዲት አገልግሎት

ሠ. የመሀንዲስና አማካሪ አገልግሎት... ወዘተ

9. <u>ማኅበራዊ የግል አገልግሎቶች</u>

ሀ. የመንግሥት አስተዳደርና መከላከያ

ለ. የትምህርት አገልግሎት

ሐ. የጤና አገልግሎት

መ. የሙያ ማኅበራት...ወዘተ

10. <u>መዝናኛና የባህል አገልግሎት</u>

ሀ: የሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት

ለ. ቴያትር አገልግሎት...ወዘተ

11. <u>የግልና የቤተሰብ አገልግሎት</u>

ሀ. የጫማ አዳሽ

ለ. የኤሌክትሪክ ዕቃዎች አዳሽ

ሐ. ፀጉር አስተካካይ...ወዘተ

12. <u>ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ኤምባሲዎች</u>

ሀ. የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን

ለ. የአፍሪካ አንድነት ድርጅት

ሐ. ኤምባሲዎች

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምሳሌዎች መሠረት ግለሰቡ የሚሠራበት ድርጅት ዋና ምርት፣ ወይም የንግድ ዓይነት ወይም የአገልግሎት ዓይነት በዓምድ 35 በተሰጠው ባዶ ቦታ ይመዘገባል:: ነገር ግን ከ64–65 ባሉት ካርድ ኮለሞች መንም አይሞላም::

ዓምድ 36 የቅጥር ሁኔታ

የሥራና የድርጅቱ ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ለተሞላላቸው የቤተሰቡ አባላት ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘረው መሠረት የቅጥር ሁኔታ ተጠይቆ በዓምድ 36 በአጭር ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 67 ትክክለኛ ኮድ ይሞላል::

የቅጥር ሁኔታ ዝርዝር ኮድ

0 = ቀጣሪ፣ አንድ አባል በግሉ የራሱን ሥራ የሚያካሂድ ከሆነና በድርጅቱ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ የበለጡ ሠራተኞች ቀጥሮ የሚያሠራ ሲሆን ነው::

1 = ለመንግሥት ተቀጣሪ፣ በደመወዝ ወይም በዓይነት መልክ እየተከፈለው ለመንግሥት የሚሠራ ነው::

2 = ለአምራቾች ወይም ለአገልግሎት የኅብረት ማኅበር ተቀጣሪ፣ በደመወዝ ወይም በዓይነት መልክ እየተከፈለው ለአምራች ወይም ለአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበር የሚሠራ ነው::

3 = ለግል ድርጅት ተቀጣሪ፣ በደመወዝ ወይም በዓይነት መልክ እየተከፈለው ለግል ድርጅት ወይም ለግል ቤተሰብ ተቀጥሮ የሚሠራ ነው::

4 = ለዓለም አቀፍ /ኢንተርናሽናል/ ድርጅት ተቀጣሪ፣ በኤምባሲዎች፣ በተባበሩት መንግሥታት አካል በሆኑ ድርጅቶች፣ በውጭ አገር መንግሥታት በሚካሄዱ ድርጅቶች፣ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣...ወዘተ ተቀጥረው የሚሠሩ ናቸው::

5 = የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል፣ የአምራቾች መኅበር አባል ሆኖ የሚሠራ በዚህ ይመደባል::

6 = በግል ሥራ የሚተዳደር፣ አንድ አባል በግሉ ወይም በቤተሰቡ አባላት ረዳትነት የራሱን ድርጅት የሚያካሂድ ነው:: የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበር አባላን አይጨምርም::

7 = ባይከፈለው ለቤተሰብ ድርጅት የሚሠራ፣ አንድ አባል የሚኖርበት ቤተሰብ ለሚያካሂደው ድርጅት ባይከፈለው የሚሠራ ሲሆን ነው::

8 = ሌላ /ለበጎ አድራጎት፣ ለሕዝባዊያን ድርጅት፣ ለሃይማኖት ድርጅት፣ የሥራ ስምምድ የሚያደርጉ፣...ወዘተ ባይከፈላቸው የሚሠሩ /::

ዓምድ 37—40 አሥር ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች ሁሉ የሚጠየቅ

በነዚህ ዓምዶች ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች በሕይወት የወለዱዋቸው ልጆች ብዛት ተጠይቆ ይሞላል::

በዓምዶቹ ተፈላጊ መረጃዎች ከመመዝገቡ በፊት "በሕይወት ተወለደ" የሚለውን ጽንሰ ሃሣብ በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል:: "በሕይወት መወለድ" ማለት አንድ ሕፃን እንደተወለደ ሕይወት ያለው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው:: በአጠቃላይ በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት ወንዶና ሴቶ የተወለደውን አይጨምርም::

ዓምድ 37—39 በጠቅላላ በሕይወት የወለዱዋቸው ልጆች ስንት ናቸው?

ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ የሆኑ ሴቶች በሕይወት የተወለዱ ልጆች ከሌላቸው በዓምድ 37፣ 38፣ እና 39 ባሉት ካርድ ክለፎች ውስጥ ክዶ "00" ይመዘገባል::

ዓምድ 37 አብረው የሚኖሩ

በጠቅላላው በሕይወት ከተወለዱ ልጆች ውስጥ ስንቱ እናትየዋ ካለችበት ቤተሰብ ጋር እንደሚኖሩ በመጠየቅና የልጆቹን ብዛት በጽታ በመለየት በዓምድ 37 ካርድ ክለፍ 68 እና 69 ይሞላል:: ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴቶች

ሚያዝያ 14 ቀን 1980 ዓ.ም. ይሆናል ማለት ነው:: ቤትዎ ባለፉት 12 ወራት ልጅ ካልወለደች በካርዱ ኮለም 74 እና 75 ኮዱ "0" ይሞላል::

## ክፍል — 3 ስለ ሞት መረጃ

### ዓምድ 41 — ባለፉት 12 ወራት በሞት የተለዩ የቤተሰቡ አባላት ዝርዝር

ባለፉት 12 ወራት ከቤተሰቡ ውስጥ የሞቱ መደበኛ አባላት እንዳሉ በመጠየቅ የሞቱት ግለሰቦች ሙሉ ስም በተሰጠው ቦታ ተመዝግቦ፣ ጾታና ዕድሜ ከ76 እስከ 90 ባሉት ካርድ ኮለም ለወንድ = 1፣ ለሴት = 2 ይመዘገባል:: እንዲሁም ዕድሜን በሚመለከት በተገቢው ካርድ ኮለሞች ሟቹ በሞቱበት ጊዜ የነበረው ዕድሜ በሙሉ ዓመት ይመዘገባል::

ይህ ዓምድ እስከ አምስት ለሚደርሱ የቤተሰብ አባላት የሞት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ሆኖ ተዘጋጅቷል:: ከቤተሰቡ ከአምስት በላይ አባላት ከሞቱ በዓምዱ ግርጌ ባለው ክፍት ቦታ ስለ ተጨማሪ ሞቶች መረጃ መመዝገብ አለበት::

## ክፍል — 4 ስለ መኖሪያ ቤቶች ዝርዝር መረጃ

አጠቃላይ መመሪያ — ክፍል አራት ከመሞላቱ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ያስፈልጋል::

1. በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ ቤቱን በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ ለአንደኛው ቤተሰብ ብቻ ሲሆን ለቀሩት ቤተሰቦች ግን ቤቱን የሚመለከተው የመጠይቅ ክፍል ሠረዝ "——" ይደረግበታል::
2. አንድ ቤተሰብ ከአንድ በበለጡ ቤቶች ውስጥ የሚኖር ከሆነ ቤቶቹን በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ ሁሉንም ቤቶች በማጠቃለል እንደ አንድ ቤት በመቆጠር ይሆናል::

3. ስለ ቤት መረጃ የሚሰበሰበው በቆጠራው ቀን ቤቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲኖሩበትና በከፊል ደግሞ ለሌላ ሥራ የዋለ እንደሆነ ብቻ ነው።

4. ሰው ባይኖርባቸው ሙሉ በሙሉ በቆጠራው ጊዜ ለድርጅት የዋሉ ቤቶች መጠይቁ አይሞላላቸውም።

5. በዚህ ክፍል ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ለአብዛኛዎቹ መልሱ በኮድ የሚሰጥ ስለሆነ በመጀመሪያ በትክክለኛው ኮድ ክብ ከተደረገ በኋላ ይኸው ኮድ በተገቢው ካርድ ኮለም ይመዘገባል።

6. ስለ ቤት መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት በተለይም ቤቱ አብዛኛው የተሠራው ከምንድን ነው የሚለውን በሚመለከት ግድግዳውና ጣራ የተሠራበት ዕቃ ዓይነት በሚመለከት የዕቃውን ዓይነት በጥንቃቄ አጣርቶ ትክክለኛውን መልስ መመዝገብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም መልስ ሰጪውን ለመርዳት በቤቱ ተዘዋውሮና የቤቱን ክፍሎች በሥርዓት ተመልክቶ ትክክለኛውን መልስ በተገቢው ዓምዶች መመዝገብ ያስፈልጋል።

ማሳሰቢያ

ስለቤቶች መረጃ የሚሰበሰበው ስለመደበኛ ቤተሰብ መኖሪያ ብቻ ነው።

ዓምድ 42 — ቤቱ አብዛኛው የተሠራው ከምንድን ነው?

አብዛኛው የቤቱ ግድግዳና ጣሪያ የተሠራበትን የዕቃ ዓይነት በመጠየቅ በተሰጠው መልስ ከሚከተሉት የኮድ ዝርዝሮች ዓይነት በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ ከተደረገ በኋላ ይኸው ኮድ በዓምድ 40 በካርድ ኮለም 30 ይሞላል። መልስ ኮድ 8 ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤቱ አብዛኛው የተሠራው ከምን እንደሆነ ይመዘገባል።

0 = ግድግዳው እንጨትና ሳር፣ ክዳኑ የሳር

1 = ግድግዳው እንጨትና ጭቃ፣ ክዳኑ የሳር

2 = ግድግዳው እንጨትና ጭቃ ክዳኑ እንጨትና ጭቃ

3 = ግድግዳው እንጨትና ጭቃ፣ ክዳኑ ቆርቆሮ

4 = ግድግዳው ድንጋይ፣ ክዳኑ ሳር

5 = ግድግዳው ድንጋይ፣ ክዳኑ ቆርቆሮ

6 = ግድግዳው ድንጋይ፣ ክዳኑ እንጨት፣ ጭቃ፣ ሳር

7 = ግድግዳው ድንጋይ፣ ክዳኑ እንጨት፣ ድንጋይ፣ ጭቃ፣ ሳር

8 = ሌላ /ይገለጽ/ ______

## ዓምድ 43 — ቤቱ ስንት ክፍሎች አሉት?

ክፍል ሲባል ዙሪያውን ከወለል እስከ ኮርኒሱ ወይም ጣሪያ ወይንም ሁለት ሜትር፣ በሚደርስ ግድግዳ የተከበበና ስፋቱ ቢያንስ አራት ካሬሜትር የሆነ ቦታ ሆኖ ለአንድ አዋቂ ሰው አልጋ ለማዘርጋት የሚበቃ ሥፍራ ያለው ነው። ስለዚህ የቤቱ ክፍሎች ብዛት የእንግዳ መቀበያ፣ የመኝታ፣ የሠራተኛ፣ የወጥ ቤትና ለሌላ ሥራ የሚያገለግሉ ክፍሎችንም ያጠቃልላል። የመታጠቢያና የመጸዳጃ ክፍል፣ የመተላለፊያ ኮሪደሮችና በረንዳዎች በገጠር በብዛት እንደማይገኙ ቢገመትም ቢያጋጥሙ እንደ ክፍል አይቆጠሩም።

በተሰጠው ክፍት ቦታ የክፍሎችን ብዛት በመመዝገብ ይኸው የክፍሎች ብዛት በዓምድ 41 በካርዱ ኮለም 31 እና 32 ውስጥ ይሞላል። አንድ ቤተሰብ ከአንድ ቤት በላይ ካለው በቤቶቹ የሚገኙት ጠቅላላ ክፍሎች በአንድ ላይ ተደምረው በዚህ ዓምድ ይመዘገባሉ። አንድ ቤተሰብ ለፀሎትና ለእንግዳ ማደሪያ የሚጠቀምበት አንድ የግል መስጊድ ካለው እንደ ቤተሰቡ የሚኖርበት ቤት አካል በመውሰድ እንደ አንድ ክፍል ይቆጠራል። ቤተሰቡ ከሚኖርበት ቤት ውጭ የከብቶች ማደሪያ ቤት ካለ እንደ ቤት አይቆጠርም። የቤት ቁጥርም አይሰጠውም።

ዓምድ 44፤ — የቤቱ የማድ ቤት ሁኔታ

በዚህ ዓምድ ውስጥ ቤቱ ለማድ ቤትነት ብቻ የሚያገለግል የተለየ ክፍል እንዳለው፤ ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚያውሉትን ክፍል በተጨማሪ በማድቤትነት የሚገለገሉበት እንደሆነ ወይም ፈጽሞ ማድቤት እንደሌለው በመጠየቅ በዓምዱ እንደሁኔታው ይመዘገባል። ቤቱ ማድቤት የለውም ሲባል ለማድቤትነት የተለየ ክፍል የሌለው ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚያውለውን ክፍል ለማድቤትነት ጭምር ሳያገለግል ሲቀርና ቤተሰቡ ከቤት ውጭ በሜዳ፤ በዛፍ ጥላ ሥር....ወዘተ. ምግቡን ለማዘጋጀት የሚገለገል ሲሆን ነው።

ስለዚህ የቤቱ የማድቤት ሁኔታ በመጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ኮዶች ዓይነት በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ ከተደረገ በኋላ ይኸው ኮድ በዓምድ 42 በካርድ ኮለም 33 ይሞላል።

1 = ማድቤት የለውም

2 = ለማድቤትነት ብቻ የሚያገለግል ክፍል አለው

3 = የሚያድሯበትን ቤት እንደማድቤት ይጠቀማሉ

4 = ከብቶች የሚያድሩበትን ቤት እንደማድቤት ይጠቀማሉ

ዓምድ 45 — ቤተሰቡ በሚያድርበት ቤት ውስጥ ከብቶች ያድራሉ?

ቤተሰቡ በሚያድርበት ቤት ከብቶች የሚያድሩ መሆናቸውን በመጠየቅ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ በማድረግ ይኸውም ኮድ በዓምድ 43 በካርድ ኮለም 34 ይሞላል።

1 = ያድራሉ

2 = አያድሩም

## የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ /ቅጽ4/

## አሞላል መመሪያ

ይህ ቅጽ የሚያገለግለው በቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚገኙት የመኖሪያ ቤቶች ብዛት፣ የቤተሰቦች፣ የሰዎች ብዛት በጾታ፣ በኮላሉ በሚኖሩት ሰዎች ላይ የደረሰውን የልደትና የሞት ብዛት፣ ማንበብና መጻፍ የሚችሉትና የማይችሉት ብዛትና እንዲሁም የብሔረሰብ ዓይነትና ብዛት ለማጠናቀር ነው፡፡ እነዚህ መረጃዎች የሚገኙት ከሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ነው፡፡ የቆጠራ መጠይቅ መሙላቱ ከተረጋገጠ በኋላ ወደ ቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ መተላለፍ የሚገባቸው መረጃዎች እንዲተላለፉ ይደረጋል፡፡

የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ የሚሞላው በየቀኑ ቢሆን ይኸም የቆጠራ መጠይቅ መሙላት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ቆጠራው በቆጠራ ቦታ ውስጥ እስከተጠናቀቀ ድረስ ነው፡፡

ክፍል አንድ — የአካባቢ መለያ፣

ይህ ክፍል ቆጠራው ስለሚካሄድበት ቆጠራ ቦታ አድራሻ መመዝገቢያ የሚያገለግል ነው፡፡

ዓምድ 1 እስከ 3 ክፍለ ሀገር፣ አውራጃና ወረዳ፣

የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክፍለ ሀገር፣ አውራጃና ወረዳ ስም ከዓምድ 1 እስከ 3 በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባል፡፡

ዓምድ 4 እና 5 ከተማና ከፍተኛ፣

ይህ ዓምድ አይሞላም፡፡

ዓምድ 6 የመቆጣጠሪያ ቦታ፣

ይህ ዓምድ አይሞላም፡፡

## ዓምድ 7 ቀበሌ ወይም ገበሬ ወይም ሠፈራ ጣቢያ

እንደ ሁኔታው የቆጠራ ቦታው የሚገኘው በገበሬ ማኅበር ወይም ሠፈራ ጣቢያ ውስጥ ከሆነ የገበሬ ማኅበሩ ወይም ሠፈራ ጣቢያው ስም በተሰጠው ክፍት ቦታ ተመዝግቦ ኮዱም በካርድ ኮለሞች 13 እስከ 15 ውስጥ ይሞላል::

## ዓምድ 8 — የቆጠራ ቦታ

ይህ ዓምድ አይሞላም::

## ክፍል 2 መሠረታዊ የሕዝብ ባሕሪያት ማጠቃለያ

ይህ ክፍል በቆጠራው ቦታ ስለሚኖሩት ሰዎች ብዛት በጾታ፣ ባለፉት 12 ወራት በቤተሰቡ የተወለዱ ልጆች ብዛት፣ ባለፉት 12 ወራት ከቤተሰቡ በሞት የተለዩ አባላት ብዛት፣ ማንበብና መጻፍ የማይችሉና የሚችሉ ብዛት፣ እንዲሁም የብሔረሰብ ዓይነትና ብዛት የሚመዘገብበት ነው:: ክፍል 2 መሞላት ያለበት በቅድሚያ የቆጠራው መጠይቆች በተሟላ ሁኔታ መሞላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው::

## ዓምድ 9 የቤት ተራ ቁጥር

በሕዝብና በቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 10 የቤት ተራ ቁጥር ተሞልቷል:: ስለዚህ በቅጽ 4 ዓምድ 9 በካርድ ኮለም 18 — 20 ላይ ለሚመለከተው ቤተሰብ የሚሞላው ቁጥር በሕዝብና መኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 10 የተሞላው የቤት ተራ ቁጥር ነው::

## ዓምድ 10 የነዋሪው ዓይነት

በሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 9 ካርድ ኮለም 23 የተሞላው የነዋሪ ዓይነት ኮድ በቅጽ 4 ዓምድ 10 ካርድ ኮለም 21 ላይ ይገለበጣል::

ዓምድ 11 የነዋሪ ዓይነት ተራ ቁጥር

በዓምድ 12 ለሚመዘገበ የነዋሪ ዓይነት ማለትም ለመደበኛ ቤተሰብ የቤተሰብ ኃላፊ ስም፣ ለሆቴልና ለሆስቴል ስም፣ መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች የሚያድሩበት ቦታ ስም በዚህ ዓምድ 001፣ 002፣ 003፣....ወዘተ በማለት ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል፡፡

ዓምድ 12 ስም

በዓምድ 10 በተጻፈው የነዋሪው ዓይነት ኮድና በዓምድ 11 በተጻፈው የነዋሪ ዓይነት ተራ ቁጥር አንጻር የተመለከተው መደበኛ ቤተሰብ ከሆነ የቤተሰብ ኃላፊ ስም፣ ሆቴልና ሆስቴል ከሆነ የሆቴሉና የሆስቴሉ ስም ሌላ ጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ከሆነ የጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ስም፣ እንዲሁም መኖሪያ ቤት የሌላቸው ከሆነ የሚያድሩበት ቦታ ስም ይመዘገባል፡፡

ዓምድ 13 የሰዎች ብዛት

በዓምድ 12 አቅጣጫ የተመዘገበው የቤተሰብ ኃላፊ ከሆነ የቤተሰቡ ጠቅላላ መደበኛ አባላት በጾታ በመለየት እንዲሁም የወንድና የሴት አባላት ድምር በዓምድ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ይመዘገባል፡፡ በዓምድ 12 የተመዘገበው ሆቴል፣ ሆስቴል ወይም ሌላ ጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ስም ከሆነ በሆቴሉ፣ በሆስቴሉ ወይም በሌላ ጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩት ጠቅላላ አባላት በጾታ በመለየት እንዲሁም ድምሩ ይመዘገባል፡፡ በዓምድ 12 የተመዘገበው መኖሪያ የሌላቸው ሰዎች መኖሪያ ቦታ ስም ከሆነ በጠቅላላ የሰዎች ብዛት በጾታ በመለየት እንዲሁም የወንድና ቤት ድምር ይመዘገባል፡፡

በዚህ ዓምድ የሚመዘገበው የሰዎች ብዛት የሚገኘው በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በክፍል 2 በዓምድ 15 የተመዘገቡትን አባላት በየስም አንጻራቸው በዓምድ

ያሉ ሰዎችን ብዛት በመደመር የብሔረሰብ ስም፣ ኮድ በተጻፈበት ሥር ቁጥሩ ይሰፍራል፡፡ በቆጠራው ቦታ ከ15 ብሔረሰቦች በላይ ካጋጠሙ በቅጹ ወረቀት በመቀጠል ተጨማሪዎቹን ብሔረሰቦች መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡

ድምር

ለአንድ ቆጠራ ቦታ ከአንድ ገጽ የበለጠ የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ ያስፈልጋል፡፡ እንደየሁኔታው አንድ ገጽ እንደ አለቀ ከዓምድ 13 እስከ 17 ያሉት ዓምዶች ተደምረው በቅጹ ግርጌ ድምር በሚለው ክፍት ቦታ በየዓምዶቹ ሥር ይሞላል፡፡ እዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገው እያንዳንዱ ገጽ ለብቻው መደመር ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ጠቅላላ ድምር፣

ከዓምድ 13 እስከ 17 ባሉት ዓምዶች ሥር የሚሞላው ጠቅላላ ድምር የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ በቆጠራው ቦታ ውስጥ ከተጠናቀቀና አስፈላጊዎች ሁሉ ወደ ቆጠራው ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ መተላለፋቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡ ጠቅላላ ድምሩ የሚገኘው እያንዳንዱ ገጽ ተደምሮ ድምር በሚለው አንጻር የተመዘገበውን በአንድ ላይ በመደመር ሲሆን ይኸውም በመጨረሻ በቅጹ ግርጌ ጠቅላላ ድምር በሚለው ክፍት ቦታ በየዓምዶቹ ሥር ይመዘገባል፡፡

ማስታወሻ

ከቆጠራው መጠይቅ ወደ ማጠቃለያ ቅጽ መረጃዎች በሚተላለፉበት ጊዜና እንዲሁም ሲዘጋጅ በትክክል መፈጸሙን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ዓምድ 18 ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት፣

ቆጠራው በቆጠራዉ ቦታ ከተጠናቀቀ በኋላ በቆጠራው ቦታ ውስጥ የሚኖሩት ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት በቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ በዓምድ 18 በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡ ብዛቱ የሚገኘው ከቤት፣ ቤተሰብና ድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ

ክፍል 2 ዓምድ 16 ሲሆን ይኸም የመጨረሻውን የቤተሰብ ተራ ቁጥር በመውሰድ ይሆናል። በመመዝገቢያ ቅጽ የተገኘው የቤተሰቦች ብዛት በቆጠራ ቦታ ውስጥ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ከተሞላላቸው የቤተሰቦች ብዛት መመሳከር አለበት። ካልተመሳከረ ግን የማጠቃለያው ቅጽ አሞላል ሁኔታ እንደገና በትኩረት መፈጸሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

<u>ዓምድ 19 ጠቅላላ የመኖሪያ ቤቶችና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት</u>

ቆጠራው በቆጠራ ቦታው ከተጠናቀቀ በኋላ በቆጠራ ቦታው ውስጥ ለመኖሪያ ብቻ እና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት፣ በቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ በዓምድ 19 በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል። ብዛቱ የሚገኘው በቆጠራው ቦታ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ የተሞላላቸውን መኖሪያ ቤቶች ብዛት በመቁጠር ይሆናል። ይህም የሚገኘው በቤት፣ በቤተሰብና በድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ—1 ከተመዘገቡት መደበኛ መኖሪያ ቤትና መደበኛ መኖሪያና ድርጅት /በቅጹ በዓምድ 12 ኮድ "1" እና ኮድ "2" የተሰጣቸው/ የሆኑ ቤቶች ብዛት ጋር መመሳከር አለበት።

<u>ዓምድ 20 የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ስም፣ ፊርማና ቀን</u>

በመጨረሻም የቆጠራ የማጠቃለያ ቅጽ በትኩረትና በተሟላ አኳኋን የተፈጸመ ስለመሆኑ ቆጣሪውና ተቆጣጣሪው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና ቀኑን ይሞላሉ።

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምህረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1980ዓ.ም ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 48 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሐደችበት | 1955 | 25 |
| 49 | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት | 1955 | 25 |
| 50 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 17 |
| 51 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | 1966 | 14 |
| 52 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣናቸው የወረዱበት | 1967 | 13 |
| 53 | የዕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በዓል የተከበረበት | 1967 | 13 |
| 54 | የገጠርን መሬት መንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 13 |
| 55 | የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 13 |
| 56 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያረፉበት | 1967 | 13 |
| 57 | የእናት አገር ጥሪ የተደረገበት | 1969 | 11 |
| 58 | የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ አንደኛ ጉባኤ የተካሄደበት | 1972 | 8 |
| 59 | የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. ሁለተኛ ጉባኤ የተካሄደበት | 1975 | 5 |

